ክፍል 11

የቤተክርስቲያን እድገትና ‹አናካዞ›

ምዕራፍ 26

የእድገት ቁልፎቹ፡ አናካዞ ቢያዞ እና አናይዴያ

ቤቴ እንዲሞላ ወደ መንገድና ወደ ቅጥር ውጣና ይገቡ ዘንድ ግድ በላቸው፤...

ሉቃስ 14፡23

አናካዞ ምንድን ነው?

አናካዞ ማለት በአጭሩ "ግድ ማለት" ነው። በተጨማሪም ለአንድ ሰው የአንድን ነገር አስፈላጊነት ማስረዳት፣ መገፋፋት እንዲሁም ኃይልን፣ማስፈራራትን፣ ግፊትንና ጫናን ፈጥሮና ማናቸውንም መንገድ ተጠቅሞ ለአንድ ነገር ማስገደድ ማለት ነው።

አንዳንድ ጊዜ አንዳንድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃላትን ዋና ትርጉማቸውን ለመረዳት ወደ ግሪኩ ቃል መሄድ ይኖርብናል። ምክንያቱም አዲስ ኪዳን በግሪክ ቋንቋ፣ ብሉይ ኪዳን ደግሞ በዚብሩ ቋንቋ የተጻፉ በመሆናቸው ነው። አናካዞ የሚለው ቃል ታዲያ ሲተረጎም "ግድ ማለት" ይሆናል።

ከዚህ ጋር ተቀራራቢ የሆነ ሌላ ቃል አለ፣ "ቢያዞ"

ቢያዞ ምንድን ነው?

ቢያዞ የሚለው ቃል በማቴዎስ 11 ላይ የሚገኝ ቃል ሲሆን "ኃይል መጠቀም" ወይም "ለአንድ ነገር ማስገደድ" ማለት ነው። ይህ በክርስቲያኖች ዘንድ የማላገኘው ታላቅ ነገር ነው። ከእግዚአብሔር ሥራ በስተቀር በብዙ ነገር ላይ ኃይል እንጠቀማለን። ሥራችን ላይ፣ በእጮኝነት ውስጥ፣ በትዳራችንና የወደፊታችንን ስናስብ ጉልበታሞች ነን። አገልግሎት ላይ ስንመጣ ግን ፈሪ አይጦች እንሆናለን!

በቴሌቪዥን የንግድ ማስታወቂያዎችን ስመለከት ስለሚያቀርቡት ምርት ምን ያህል መተማመን እንዳላቸው አያለሁ። ከድፍረታቸው የተነሣ ምርታቸው ምን ያህል ጥሩ እንደሆነ ለማስተዋወቅ የሚሰብ ዘፈን ሁሉ ያቀርቡበታል።

የአልኮል መጠጥ አስተዋዋቂዎች በአብዛኛው በንግዱ ዓለም ውስጥ የተሳካላቸው ናቸው። ሁላችንም ቢራና የአልኮል መጠጥ ወጣቱን ትውልድ የሚያጠፋ ገዳይ ነገር እንደሆነ እናውቃለን። በአልኮል መጠጥ ምክንያት ቤተሰብ ተበትኗል፣ ትዳሮች ፈርሰዋል፣ የመኪና አደጋዎች ደርሰዋል፤ በተጨማሪም ብዙ ዓይነት ግጭትና ጦርነት በዓለም ላይ ደርሷል። ሆኖም ግን በቋሚነት ማስታወቂያ ይሠራለታል።

ቢራ ከቁጥር በላይ ለሆኑ ሰዎች ሞትና አደጋ መንሥዔ ነው። ነገር ግን በፈገግታ የተሞሉ ሰዎች በቴሌቪዥን መስኮት ብቅ ብለው የሚያስፈልገን "ኃይል" እንደሆነ ይነግሩናል። እነዚህ የንግድ ማስታወቂያዎች ጉሮሮዋችንን ይዘው እያስገደዱን ነው። እውነት ያልሆነውን ነገር እንድናምን እየተገደድን ነው።

ምንም እንኳ ቢራ "የተበጠበጠ ዲያቢሎስ" ቢሆንም እንድናምን ግን እየተገደድን ነው።

ምንም ዓይነት ዋጋ ከፍለው ገንዘብ ማግኘት ስለሚፈልጉ ሰዎች ሳስብ፤ ክርስቲያኖች በኃይል ለመነሣት እጅግ የተሻለ ምክንያት እንዳላቸው እገነዘባለሁ። ታዲያ እኛ ክርስቲያኖች እግሯ እንደተሰበረ ዳክዬ፣ ጥርስ እንደሌለው ውሻ ወይም አንደ አቅመ ቢስ ድንቢጥ ወፍ የምንሆነው ለምንድን ነው?

ነገር ግን የአናካዞ እና የቢያዞ መገለጥ ይህንን እንደሚለውጥ አምናለሁ። ቢያዞ ማለት ለአንድ ነገር ማስገደድ ማለት ነው። ክርስትናን ለማሰራጨት ከዚህ በበለጠ ሁኔታ ኃያላን መሆን ይጠበቅብናል።

ገንዘብ ለማግኘት፣ የሐሰት ሃይማኖትን ለማስፋፋት ወይም ገዳይ የሆኑ ምርቶችን ለመሸጥ ዓለም በኃይል እየተንቀሳቀሰች ነው። ክርስቲያኖችም መጽሐፍ ቅዱሳዊ በሆነ መልኩ ጉልበታም መሆን አለብን ብዬ የማስተምረው ለዚህ ነው።

አናይዴዳ ምንድን ነው?

ሌላ ከዚህ ጋር ተያይዞ እንድናጠና የምፈልገው የግሪክ ቃል አናይዴዳ የሚለውን ነው። አናይዴዳ የሚለው የግሪክ ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንዴ ብቻ የተጠቀሰ ሲሆን ትርጉሙም "ይሉኝታ ቢስ"

ማለት ነው። በሉቃስ ወንጌል በ11ኛው ምዕራፍ ውስጥ ከእግዚአብሔር ጋር ባለው ጎብረት "ይሉኝታ ቢስ" ሆኖ የታየ ሰው አለ።

> አላችኋለሁ፥ ወዳጅ ስለ ሆነ ተነሥቶ ባይሰጠው እንኳ፥ ስለ ንዝነዛው (አናይዴዳ) ተነሥቶ የሚፈልገውን ሁሉ ይሰጠዋል።
>
> ሉቃስ 11፡8

በ1982 በአገሬ ታዋቂ ወደሆነው የጋና ዩኒቨርሲቲ ገባሁ። ወደዚህ አዲስ ድባብ በቀስታ በምገባበት ጊዜ ምን ይገጥመኝ ይሆን ብዬ ማሰቤ አልቀረም። ታዲያ አንድ ያስደነገጠኝ ነገር ቢኖር የኢአማኒያን ይሉኝታ ቢስ መሆን ነበር።

የሚሳሳሙ ተማሪዎች

ከዕለታት አንድ ቀን ቮልታ ሆል ተብሎ ወደሚጠራው የሴቶች አዳራሽ አመራሁ። የመጀመሪያውን ደረጃ ወጥቼ ሁለተኛውን ስጀምር ኮሪደሩ ጥግ አንድ ወንድና ሴት ጥብቅ ብለው ተቃቅፈው ይሳሳማሉ። በእርግጥ ይህ በአንዳንድ ስፍራ ምንም እንዳልሆነ እንደሚቆጠር አውቃለሁ። ሆኖም ግን ለእኔ እንግዳ ነገር ነበር።

በዚያ በማልፍበት ጊዜ እነዚህ ጥንዶች ረዘም ላለ ጊዜ ተቃቅፈው እየተሳሳሙ ቆይተዋል። ማንም ቢያያቸው ግድ አልነበራቸውም! አልተንቀሳቀሱም! ይሉኝታ ቢሶች ናቸው። ምናልባት በፍቅር እንደወደቁ ተሰምቷቸዋል።

ላይኛው ፎቅ ስደርስ ለጓደኞቼ፣ "በዚህ አካባቢ ያሉ ሰዎች ምንም ዓይነት ይሉኝታ አይሰማቸውም" አልኋቸው።

ከዚያም እንዲህ ስል ጠየቅሁ፣ "ስለምናምነው ነገር ስለምን እናፍራለን?"

በወንጌል ለምን እናፍራለን?

ምንም ልናቀርበው የምንችለው ነገር የሌለን ዓይነት ፈሪ አይጦች መስለን ለምን እንንቀሳቀሳለን?"

የእግዚአብሔር መንፈስ በውስጤ ተነሣና እንዲህ አልሁ፣ "እነርሱ ሥነ-ምግባር በራቀው ሕይወታቸው ካላፈሩ፣ እኔም በወንጌል አላፍርም።"

በወንጌል አላፍርምና፤ . . .

ሮሜ 1፡16

ግብረ ሰዶማውያን በድፍረት ብልሹ ስለሆነው የሕይወት ዘዴአቸው ይናገራሉ። በቴሌቪዥን መስኮት እየታዩ በመቀመጫ በኩል ስለሚያደርጉት የግብረ ሥጋ ግንኙነት ሲለፍፉ ሐፍረት አይሰማቸውም። እነዚህ ሰዎች በኃይል መብታቸውን ለማስከበር ይጣደፋሉ። ክርስቲያኖች ታዲያ የእግዚአብሔርን ቃል ለመናገር አፋችን የሚለጎመው ለምንድን ነው?

ብዙ ክርስቲያኖች ቢሮአቸው ተቀምጠው የማያምኑ የሥራ ባልደረቦቻቸው ክፉ ድርጊቶቻቸውን ያለ ሐፍረት እንዲተርኩላቸው ይፈቅዱላቸዋል። በዙሪያችን ያሉ ኢአማኒያን በውይይት ጊዜ በማይረቡ ቃላት ተጽዕኖ እንዲፈጥሩብን እንፈቅድላቸዋለን።

ሐዋርያው ጳውሎስ ግን አናይዴያን ተለማምዶ ነበር። አስታውስ፣ ይህንን ያለው ሐዋርያው ጳውሎስ ነው፤ "በወንጌል አላፍርምና!"

ብዙ ክርስቲያኖች ሊያካፍሉት የሚችሉት የታመነና እውነተኛ መልእክት አላቸው። በጎ ተጽዕኖ መፍጠር ግን ይችል ዘንድ አስገዳጅ መሆን ይኖርበታል። ሰሚውን እንዲለወጥ የሚገፋፋ መሆን ይኖርበታል። የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ መልእክት ያልዳኑትን፣ ክርስቶስን የግል አዳኛቸው አድርገው እንዲቀበሉ የሚገፋፋ ነው። ስለዚህም የአናካዞን፣ የቢየዞንና የአናይዴዳን መልእክት መያዝ ይኖርብናል።

ምዕራፍ 27

ለቤተክርስቲያን እድገት የአናክዘ አስፈላጊነት

በሉቃስ ወንጌል አስራ አራተኛው ምዕራፍ ላይ ኢየሱስ ለጓደኞቹ ግብዣን ስላደረገ ሁነኛ ሰው የተናገረውንና የምናውቀውን ታሪክ እናነባለን። ከዚህ ታሪክ ጋር በሚገባ መግባባት እንደትችል ሙሉውን ታሪክ እንድታነበው አፈልጋለሁ።

እርሱ ግን እንዲህ አለው፦ አንድ ሰው ታላቅ እራት አድርጎ ብዙዎችን ጠራ፤

በእራትም ሰዓት የታደሙትን። አሁን ተዘጋጅቶአልና ኑ እንዲሉአቸው ባሪያውን ላከ።

ሁላቸውም በአንድነት ያመካኙ ጀመር። የፊተኛው። መሬት ገዝቼአለሁ ወጥቼም ላየው በግድ ያስፈልገኛልና፤ ይቅር እንድትለኝ አለምንሃለሁ አለው።

ሌላውም። አምስት ጥምድ በሬዎች ገዝቼአለሁ ልፈትናቸውም እሄዳለሁና፤ ይቅር እንድትለኝ አለምንሃለሁ አለው።

ሌላውም። ሚስት አግብቼአለሁ ስለዚህም ልመጣ አልችልም አለው።

ባሪያውም ደርሶ ይህን ለጌታው ነገረው። በዚያን ጊዜ ባለቤቱ ተቆጥቶ ባሪያውን። ወደ ከተማ ጎዳናና ወደ ስላች ፈጥነህ ውጣ ድሆችንና ጕንድሾችን እንኳሶችንና ዕውሮችንም ወደዚህ አግባ አለው።

ባሪያውም። ጌታ ሆይ፥ እንዳዘዝኸኝ ተደርጎአል፥ ገናም ስፍራ አለ አለው።

ጌታውም ባሪያውን። ቤቴ እንዲሞላ ወደ መንገድና ወደ ቅጥር ውጣና ይገቡ ዘንድ ግድ በላቸው፤

አላችኋለሁና፥ ከታደሙት ከእነዚያ ሰዎች አንድ ስንኳ እራቴን አይቀምስም አለው።

ሉቃስ 14፡ 16-24

ይህ ሰው እንዳለመታደል ሆኖ ታላቅ ግብዣ ለማድረግ ብዙ ገንዘብ አውጥቷል፣ ዋና ዋና ሰዎችን ጋብዟል። ሆኖም ግን አብዛኞቹ አልመጡም። ይህ ሰው ግብዣውን ስላቃለሉበት ተገርሟል። የጋበዛቸውን ሰዎች ሰበብ ሲሰማ ተቆጣ። ስለዚህም በመንገድ ላይ የሚገኙትን ማናቸውንም ሰዎች ለመጋበዝ ወሰነ።

እስቲ አስበው፣ የማያውቃቸውን ሰዎች ወደዚህ ግብዣ ሲጠራ!

ሆኖም ግን በአጋጣሚ በዚያ ምሽት ብዙ ሰዎች በመንገድ ላይ አልነበሩም። ምንም እንኳ የተወሰኑት ከመንገድ ተጠርተው ግብዣው ላይ ቢታደሙም በአንጻራዊነት ተጋባዦቹ ገና ጥቂቶች ነበሩ። በኋላ ግን የታመሙትን፣ ዓይነስውራንንና አካል ጉዳተኞችን ሊጋብዝ ቁርጥ ውሳኔ አደረገ። በዓይነ ሕሊናህ አስበው! ምን ዓይነት ያልተለመዱ ተጋባዦች ናቸው! ግብዣው ከሰው ተራ በማይገቡ፣ ጎብረተሰቡ አንቅሮ በተፋቸው ሰዎች ተሞላ።

በሉቃስ አማካኝነት ማደግ

ይህ ተምሳሌታዊ ታሪክ ኢየሱስ ወደ እርሱ ሰዎችን እንድንጋብዝ እንደላከን ያሳያል። በተጨማሪም መጋቢያን አባሎቻቸውን ወደ ዓለም ሁሉ እንዲሄዱና የምስራቹን እንዲሰብኩ መላክ እንዳለባቸው ያሳያል። ሁል ጊዜም የወንጌል ስርጭት (ብዙ ሰዎችን ወደ ታላቁ የእራት ግብዣ) ላደርግ ስል የሚገጥመኝ ነገር ይህ ሰው የገጠመው ነገር ነው። ይህ ሰው ግን እንደተሳካለት አምናለሁ።

የፈለገው ነገር ሁሉ ባይሆንም፣ ግብዣውን ማድረግ ብሎም ቤቱን በእንግዶች መሙላት ችሏል። ምንም እንኳ አስቀድሞ እንዳሰበው ባይሆንም ግብዣውን ግን ማድረግ ችሏል።

ታያለህ፣ እግዚአብሔር ዓለም ሁሉ ክርስቶስን ወደ ማወቅ ይመጣ ዘንድ ቤተክርስቲያንን እንድትጋብዝ ልኳታል። ሆኖም የተጋበዙት ብዙዎቹ ምላሽ ሊሰጡ አልቻሉም። ጌታን አስቀድመው እንዲያውቁ የተጋበዙት አይሁዶች ናቸው። ሆኖም ክርስቶስን ገሸሽ በማድረጋቸው ግብዣው ወደ አሕዛብ ተላለፈ።

ብዙ በከተማ መሐል የሚኖሩ፣ ወንጌልንም በቤተክርስቲያንና በቴሌቪዥን የመስማት እድል ያላቸው እውቅ ሰዎች አሉ። ሆኖም መልእክቱን ከመቀበል ይልቅ ሰባኪያንን ሲተቹ ይገኛሉ። በመቀጠልም ወንጌል ለድሆችና ምስኪኖች ይሰበካል። ያን ጊዜ እነዚህ ሰዎች ከእግዚአብሔር ውጪ ሌላ ተስፋ የሌላቸው ስለሆነ በፈቃዳቸው ቃሉን ሲቀበሉ ይገኛሉ።

1. **አናካዞ አስፈላጊ የሚሆንበት ምክንያት ለቤተክርስቲያን እድገት ወንጌል ስርጭት አስፈላጊ በመሆኑ ነው።**

ሰዎች አናሳ በሆኑ የቤተክርስቲያን የጥሪ ልምምዶች እግዚአብሔርን ለማወቅ አይሳቡምም፣ አይገደዱምም። ቀለል ያሉት የጥሪ ስልቶቻችን በአሁኑ ጊዜ ብዙም አያስኬዱንም። ነገር ግን ወጥተን ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር ገፍተን ልናመጣቸው ይገባል።

2. **የአናካዞ አስፈላጊነት ምክንያቱ ባዶ ቤተክርስቲያናችንን የሚሞሉት ሰዎች በግብኛ ካርድ የሚመጡ ባለመሆናቸው ነው።**

ሰዎች በወንጌል እንዲነኩ አዲስ ስልት መቀረጽ አለበት። ተራራው ዝቅ ሊል፣ ሸለቆውም ሊሞላ ያስፈልጋል። በቤተክርስቲያን ተቀምጦ ሰዎችን መጋበዝ ለቤተክርስቲያን እድገት የማይጠቅምና ሊሠራ የማይችል ስልት ነው።

3. **የተወደድህ መጋቢ ሆይ፣ ያለ አናካዞ ቤተክርስቲያንህ ባዶ ትሆናለች።**

እባክህን ልብ በል፣ ይህ ሰው የአናካዞን ስልት ተግባራዊ ባያደርግ ኖር ባዶ ቤት ታቅፎ ይቀመጥ ነበር። ይህን አትርሳ "መጋቢ ያለ አናካዞ ባዶ ቤተክርስቲያን" ነው።

4. **ያለ አናካዞ ብዙ ቤተክርስቲያናት ተፈጥሮአዊውን ሞት ይሞታሉ።**

አንድ መረዳት የሚገባህ ነገር የቤተክርስቲያን አባልነት እንዲህ ነው ልትለው የማትችለው ነው። ብዙ ሰዎች ይመጣሉ ደግሞም ብዙዎች ይሄዳሉ። ታዲያ ከሚመጡት ይለቅ የሚለቁት ከበለጡ ቀስ በቀስ ቤተክርስቲያንህ እየሞተች ትሄዳለች። ቤተ ክርስቲያንህ እንዳትዘጋ የምትፈልግ ከሆነ ኢየሱስ ያዘዘውን ማድረግ ይኖርብሃል - ውጣና አናካዞን ተለማመድ።

5. ሕይወት በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን በሥራ የተወጠረች ስትሆን ሰዎችም ባተሌዎች ናቸው።

ባተሌ ሰዎች ብዙ ሰበቦች አሏቸው። የአናካዞ ስልት ታዲያ እነዚህን ሰበቦች እንድታሸንፍ ይረዳሃል። በዚህ አዲስ ግፊትና ኃይል በተሞላው አስተሳሰብህ ብዙ ሰዎችን ወደ ክርስቶስና ወደ ቤተክርስቲያን ማምጣት ይቻልሃል።

ምዕራፍ 28

አናካዞን ለቤተክርስቲያን እድገት እንዴት ማስረጽ እንደሚቻል

1. *አናካዞን ለታላቁ የእራት ግብዣ ዝግጅት ተጠቀምበት*

ማንም የቤተክርስቲያንን እድገት ቢሻ ሊዘጋጅ ያስፈልገዋል። ብዙ የክርስቲያን ስብከት ጣቢያዎች ብዙ ዝግጅት ካልተደረገባቸው ስኬትን ማግኘት አይቻልም። ለምትሠራው ነገር ሁሉ ምን ያህል ዝግጅት እንደምታደርግ ራስህን ጠይቅ። ብዙ ዝግጅትን ማድረግ ከቻልህ ብዙ ስኬትን ትጎናጸፋለህ። የጀማ ስብከቶች፣ የቤተክርስቲያን እድገት እንዲሁም ስብከት ጣቢያዎች በዝግጅትህ ይወሰናሉ። ይህ የአናካዞ ሰው ታዲያ ለታላቁ መርሐ ግብር ራሱን ያዘጋጃል።

ያለ ሺህ ሰዓታቶች ዝግጅት አገልግሎት የማይሞከር ነው። ከጥቂት ዓመታት በፊት ለአስር ሰዎች ስሰብክ የነበረው መልእክት ዛሬ ለሺዎች የምሰብከው ነው።

በትንሽ ጎብረት ማለትም በአስር ሰዎች መካከል ስሰብክ የነበረበት ጊዜ እግዚአብሔር እኔን ከሚያዘጋጅበት አንዱ ክፍል ነው። እግዚአብሔር በኃይል እንዲጠቀምብህ የምትፈልግ ከሆነ ዛሬ መዘጋጀትን መጀመር ይኖርብሃል። እያንዳንዱን እድል በቤተክርስቲያን ውስጥ ጠቃሚ ነገርን ለማድረግ አውለው።

በቤተክርስቲያኔ ውስጥ ከዓመታት በፊት ድራምና ፒያኖ የምጫወተው እኔ ነበርሁ። ምንም እንኳ በዚያን ጊዜ ያን ያህል ባልረዳውም ለአገልግሎቴ ከምዘጋጅበት አንዱ ክፍል ነበር። በአሁኑ ወቅት ስለ ሙዚቃና ስለ ሙዚቃ መሣሪያ ጠንቅቄ አውቃለሁ። አሁን ሙዚቃን፣ አምልኮንና ውድ ስለሆኑ ሙዚቃ መሣሪያዎች በእውቀት መወያየት እችላለሁ። ከሙዚቃው ክፍል ጋር ተያይዞ ያለኝ ልምድ ዋጋ ያለው እውቀት እንዲኖረኝ አድርጓል።

2. ብዙ ሰዎች ላይ በጎ ተጽዕኖ ለማምጣት አናክዞን ተጠቀም።

ይህ በሉቃስ 14 ላይ የምናገኘው ሰው ብዙ ሰዎችን ታላቅ ራት ጋብዟል። ቤተክርስቲያናት አንዱና በዋናነት የማያድጉበት ምክንያት ክርስቲያኖች ለራሳቸው ስለሚይዙት ነው። ለኢየሱስ ክርስቶስ ውጤታማ ምስክር ለመሆን ከፈለግህ ክርስትናን ለራስህ ብቻ መያዝ የለብህም።

አውቶብስ ውስጥ ገብተህ በምትቀመጥበት ጊዜ በአጠገብህ ካሉት ጋር ወዳጅነት ልትመሠርት መወሰን ይኖርብሃል። በአጠገብህ ካሉት ጋር ማውራት ጀምር። ሁልጊዜ ወንጌልን በአጠገቤ ካሉት ጋር መካፈል እሞክራለሁ። ሁልጊዜም ስለ ኢየሱስ የምናገረው መልካም የምስራች አለኝ። እርሱ አድኖኛል፤ ደግሞም ነፃ አውጥቶኛል።

በሕክምና ትምህርት ቤት ውስጥ የሁለተኛ ዓመት ተማሪ ሳለሁ፣ ባማረ ካምፓስ ውስጥ እንኖር ነበር። በየዕለቱ ታዲያ በሌላኛው የከተማው ጥግ ወደ መማሪያ ሆስፒታሉ እንጓዝ ነበር። ከጥግ እስከ ጥግ ለመሄድ ደግሞ የአንድ ሰዓት ጊዜ ይወስዳል።

ፊኛዎችና ኮንደሞች

አንድ ቀን በአውቶብስ ውስጥ ተቀምጬ በትምህርት ቤቱ በቆይታ የሚበልጡኝ ተማሪዎች የሚሠሩትን እመለከት ነበር። ኮንደም እንደ ፊኛ እየነፉ ካሰሩ በኋላ በአውቶብሱ መስኮት ይለቅቁና ይሳሳቁ ነበር። እነዚህ ተማሪዎች ሲጫጫሁና በማይረባ ቀልዳቸው ሲዝናኑ እንዴት በሥራቸው እንደሚተማመኑና ሐፍረትም እንደማይሰማቸው አስተውያለሁ። እኛ ክርስቲያኖች ደግሞ በፍርሃት ተሸብበን መጻሕፍቶቻችን ላይ ብቻ አትኩረን ተቀምጠናል።

ያን ቀን ዝም ላለማለት ወሰንሁ። በአውቶብሱ ውስጥ ያሉትን የእያንዳንዱን ትኩረት ካገኘሁ በኋላ መስበክ ጀመርሁ። ምንም እንኳ በኋላ ላይ በአውቶብስ ውስጥ መስበክ የተለመደ ቢሆንም ያን ጊዜ ግን እንግዳ ነገር ነበር። የተወሰኑት ተማሪዎች ሲቆጡ ሌሎች ደግሞ የመሰላቸት ሁኔታ አሳዩ።

አንዳንዶች ደግሞ የምሰብከውን እንደማይቀበሉ ለማሳየት በመስኮት አሻግረው ማየት ጀመሩ። እኔ ግን ስብከቴን ቀጠልሁ! ለራሴ ብቻ

ላልይዘው ቆርጫለሁ። በሉቃ 14 ላይ ያለውን ሰው ልመስል ወስኛለሁ።

በለንደን አውቶብስ ውስጥ ማጨብጨብ

አናካዞአዊ ሰው የያዘውን ለራሱ ይዞ ዝምታን አይመርጥም። ለተወሰነ ጊዜ ያህል በለንደን ኖሬያለሁ። የትም ቢሆን በሁሉም ስፍራ እሰብክ ነበር። በእንግሊዝ ውስጥ ግን በቀላሉ ከሰዎች ጋር መግባባት አልቻልሁም። በዚያ ያለው እያንዳንዱ ሰው መግባባት የማይፈልግና ግድ የሌለው ይመስላል።

አንድ ቀን ባለ ድርብ መቀመጫ አውቶብስ ውስጥ ተቀምጬ እየተጓዝሁ ሳለሁ፤ የአናካዞ መንፈስ በውስጤ ተነሣና ለራሴ እንዲህ አልሁ፤ "ከዚህ በኋላ ዝም ማለት አይኖርብኝም።"

በእግሬ ድንገት ቆምሁና በአውቶብስ ውስጥ ያሉት ሁሉ በአድናቆት እያዩኝ፣ የእያንዳንዳቸውን ትኩረት ለማግኘት በእጆቼ አጨበጨብሁ። ከውጭ ስታይ ደፋር ብመስልም በውስጤ ግን በፍርሃት ርዳለሁ።

በአውቶብስ ውስጥ ያሉት አብዛኛዎቹ ጨካኝ ፊታቸውን አሳዩኝ። እኔ ግን በፍጹም መረጋጋት የወንጌልን መልእክት አቀረብሁ።

ለጥቂት ደቂቃዎች የዚህን እብድ ወጣት ስብከት ለማዳመጥ አውቶብሱ ውስጥ ጸጥታ ሰፈነ። ከስብከቱ በኋላ ተቀመጥሁና የሚቀጥለው መቆሚያ ላይ ወረድሁ። ከእኔ ጋር የወረዱ አንድ ትልቅ ሰው እንዲህ አሉኝ፣ "ድፍረትህን አደንቃለሁ! ብዙ ርቀት ግን የምትሄድ አይመስለኝም።" ዋናው ነገር ብዙ ርቀት መሄዴ አለመሄዴ አይደለም። ዋናው ነገር ቃሉን መስበኬ ነው። ቃሉ በሚሰበክበት ጊዜ ደግሞ አንድ ነገር ይፈጸማል ‹‹...ከአፌ የሚወጣው ቃል...የምሻውን ሳይፈጽም በከንቱ ወደ እኔ አይመለስም...›› (ኢሳይያስ. 55፡11)።

3. *አናካዞን ተጠቀም፣ አገልግሎትህን አትሰርዝ። ማንም አናካዞን የሚለማመድ ቢኖር አገልግሎቱን ለመሰረዝ ዝግጁ አይደለም።*

የትኛውም መጋቢ፣ በመደበኛ የቤተክርስቲያን እድገት ውስጥ በሚያልፍበት ጊዜ ከፍታዎችንና ዝቅታዎችን ይለማመዳል።

ነገር ግን የአናካዞን መንፈስ የያዘ መጋቢ የቤተክርስቲያንን አገልግሎት አይሰርዝም። ምንም ያህል ሰዎች በቤተክርስቲያን ውስጥ ይገኙ በጽናት አገልግሎቱን ያገለግላል።

ከመጋቢዎቹ አንዱ በአንድ በተለየ እሁድ ዕለት አንድ ሰው ብቻ በቤተክርስቲያን ውስጥ እንደተካፈለ ነግሮኛል። መጋቢው በፍጹም የወረደ መንፈስ እንዳልተሰማው ነግሮኛል። ይልቁንም ለዚያ ለአንድ ሰው በመስበክ የሚቻለውን ለጌታ አድርጓል።

ሐናንያ በማኅበረሰብ ውስጥ

አንድ ጊዜ አስታውሳለሁ፣ ከአገልግሎታችን በአንዱ በጣም ጥቂት ሰዎች ብቻ ይካፈሉ ነበሩ። ጌታም በሉቃ. 14 ላይ እንዳደረገው ሰው እንዳደርግ ተናገረኝ፡ "ወደ ውጪ ውጣና ኅብረተሰቡን ወደ ቤተክርስቲያን ጋብዝ።"

"በእሁድ ቀን ይህንን እንዴት አደርጋለሁ?" ጌታም መለሰልኝ፣ "ይህንን ብታደርግ ትባረካለህ።"

ከጌታ ጋር መከራከሬን ቀጠልሁ፣ "የእሁድ ጠዋት ጎብኚዎቻችን ምን ያስባሉ?" "ሰዎችን እኮ ከቤተክርስቲያን እያባረርናቸው ነው።"

እግዚአብሔር ግን አጥንክሮ፣ "ውጣና እንዲመጡ ግድ በላቸው" አለኝ።

እኔም ታዘዝሁ።

የአምልኮ ጊዜውን እንድናቆምና ማኅበረሰቡን እንድንጋብዝ አሳሰብሁ።

ማሳሰቢያዬን ቀጠልሁ "የምናደርገው ቀላል ግብዣ አይደለም። እያንዳንዱ ሰው የአንድ ሰው እጅ ይዞ መታየት ይኖርበታል። በግልጽ ወደዚህ የቤተክርስቲያን ሕንፃ ሰው ይዛችሁ እንድትመጡ።"

አንዳንዶች ወደ ሁዋላቸው አፈገፈጉ። እኛ ግን አደረግነው። በመቶ የሚቆጠሩ በማኅበረሰቡ ውስጥ የነበሩ "በቤተክርስቲያን ያልታቀፉ" ሰዎች መጡ። በዚያ ቀን ብዙዎች ሕይወታቸውን ለክርስቶስ ሰጡ። ይህንን በተወሰነ ጊዜ ከፋፍለን ደጋግመን አደረግነው። ያ አገልግሎት በሚያስገርም ሁኔታ ሰፋ፣ አደገ። ምንም እንኳ የተካፋዮች ቁጥር

አነስተኛ ቢሆንም ልዘጋው አልፈለግሁም። የትኛውም የአናካዞ መንፈስ ያለው መጋቢ ይህንን ለማድረግ ዝግጁ መሆን አለበት።

4. *አናካዞን* በመጠቀም አዳራሾች ባዶ እንዳይሆኑ ተከላከል።

የአናካዞ መንፈስ ያለው መጋቢ ባዶ የቤተክርስቲያን አገልግሎት እንዲኖር አይፈቅድም። ከብዙ ዓመታት በፊት የሕክምና ተማሪ ሆኜ ጌታ ቤተክርስቲያን እንድተክል ተናገረኝ። በቤተክርስቲያኔ ውስጥ አባላት አልነበሩኝም። አንድም የምሰብከው ሰው አልነበረም! ሆኖም ግን ባዶ ቤተክርስቲያን እንዲኖረኝ ፈቃዴ አልነበረም።

አናካዞ እና የማለዳ የወንጌል ምስክርነት አዋጅ

መንፈስ ቅዱስ ወደ ነርሲንግ ተማሪዎች መኖሪያ በመራኝ ጊዜ ተማሪ ነበርሁ። ያን ቀን ከንጋቱ 11፡00 ሰዓት ሲሆን ገና ጨለማ እንደነበር አስታውሳለሁ። ከመኖሪያቸው ውጪ ላይ ቆሜ አጨብጭቤ ቀሰቀስኋቸው። ሲያዩኝ ገርሟቸዋል። እኔ ግን ምንም አልመሰለኝም። ስለ ኢየሱስ ሰበኩላቸው። ስጨርስ በድፍረት እንዲህ አልኋቸው "ሕይወታችሁን ለክርስቶስ መስጠት የምትፈልጉ ከሆነ የለሊት ልብሳችሁን ቀይሩ። የተገባ ልብስ ልበሱና ምድር ቤት ኑ፤ ስለ ክርስቶስ ልንነግራችሁ እንፈልጋለን።"

በዚያ ማለዳ ብዙ ወጣት ሴቶች ሕይወታቸውን ለእግዚአብሔር ሰጡ። እስከዛሬም ድረስ ብዙዎቹ በቤተክርስቲያናችን ውስጥ አባላት ናቸው።

ለሰዎች ከአልጋቸው ሳይነሡ በማለዳ መስበክ ለእኔ የአናካዞን መርህ የምተገብርበት የምወደው መንገድ ነው። አንድ ማለዳ ላይ ለሕዝብ የጤና ነርሶች በመኖሪያቸው ውስጥ እየሰበክሁ ነበር። በመሃልም ከአንዲት ሴት ደክማ ወደ ሁዋላ የተመለሰች እንደሆነችና እርዳታችንን እንደምትሻ በቁራጭ ወረቀት ጽፋ ነገረችን። በዚያ ማለዳ እርሷን አገለገልናት እግዚአብሔርም ነፃ አወጣት። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ላለፉት 10 ዓመታት የቤተክርስቲያናችን ታማኝ አባል ናት።

ምንም እንኳ ስጀምር በባዶ የመማሪያ ክፍል ውስጥ ቢሆንም ወዲያው ግን በማለዳው የአናካዞ የወንጌል እወጃ አማካኝነት ቤቱ ሕይወታቸውን ለጌታ በሰጡ ነርሶች አማካኝነት ተሞላ።

አንባቢዬ ሆይ፣ አንድ እንድትረዳ የምፈልገው ነገር አለኝ። ቤተክርስቲያንን ከማንም አልወረስሁም። ብዙ ጊዜ ማንንም ወደማላውቅበት እኔም ወደማልታወቅበት ስፍራ ተጉዣለሁ። ቤቱ እስኪሞላ ድረስ መውጣት፣ ነፍሳትን ለጌታ ለመማረክ ሰዎችን ስለ ጌታ ግድ እል ነበር።

5. የሰዎችን ሰበብ ለማሸነፍ *አናግዘን* ተጠቀም።

ብዙ ሰዎች በሰበብ የተሞሉ ናቸው። በታሪኩ ውስጥ የምናየው ሰው ወደ ግብዣው ከተጋበዙት ሰዎች ሦስት አስደናቂ ሰበቦች ቀርበውለታል። ጋባዡ በአንዱም ግን ሲመሰጥና ሲሳብ አናይም።

አንደኛው የቀረበለት ሰበብ በምሽት በሬዎችን ሊፈትን እንደሆነ ነው። በዚያ ምሽት ማንም በሬዎቹን ሊፈትን እንደማይችል ማንም ያውቃል።

የሁለተኛው ሰበብ ደግሞ ጋብቻ ነው። ማንም ሊረዳው እንደሚችለው ራት ለአዲስ ተጋቢዎች ጥሩ ነገር ነው።

የሦስተኛው ሰበብ በዚያ ምሽት መሬት ሊያይ እንደሚሄድ ነው። አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ። አንድ መሬት ከመግዛትህ በፊት መሬቱን በሚገባ አታየውምን? አንድን መሬትስ በምሽት በሚገባ ማሰስ የምትችለው እንዴት ነው? በሚገባስ ይታይሃልን? ሆኖም ግን አንድ ሰው ግብዣን የሚያህል ነገር ላለመቀበል በሰበብነት ተጠቅሞበታል።

የትኛውም ሰዎችን በወንጌል መድረስ የሚሻ መልካም አገልጋይ በሰዎች ሰበብ መያዝ አይኖርበትም። የሰዎችን ሰበብ ለማሸነፍ መማር ይኖርበታል።

በእግዚአብሔርም ቃል በምታገለግልበት ጊዜ ሰዎች በአእምሮዋቸው ውስጥ የተሰያዩ ሰበቦችን ያቀርባሉ። ቃሉን ለምን እንደማይታዘዙ ምክንያቶችን ይደረድራሉ። እያንዳንዱ መልካም ሰባኪ የሰዎችን ሰበብና አስተሳሰቦች ጥሶ ማለፍ አለበት። ኢየሱስ የሰዎችን ሰበብና ሐሳብ ጥሶ ይናገር የነበር ሲሆን እነርሱም ያንን ያውቃሉ!

. . ይህን ምሳሌ በእነርሱ ላይ እንደ ተናገረ አወቀው።

ሉቃስ 20፡19

ብዙ ሰበቦች ተጨባጭ ምክንያቶች የላቸውም። በጎ አገልጋይ በባዶ ሰበቦች ውስጥ አሻግሮ ማየት ይኖርበታል። ለአንድ ወዳጄ ወደ ቤተክርስቲያን እንዲመጣ ግብዣ አደረግሁለት። እርሱ ግን እንዴት ጊዜው እንደማይመቸውና መኖሪያውም ከቤተክርስቲያን ምን ያህል እንደሚርቅ መናገር ጀመረ።

እኔም እንዲህ አልሁት "አንተ የተሳካልህ ነጋዴ ነህ። ማድረግ የምትፈልገውን፣ ታደርጋለህ። ብዙ ስፍራዎች ትጓዛለህ። በየማለዳው ትነሣለህ።

አንድ መቶ ኪሎ ሜትሮች ያህል ርቃ የምትገኘውን የሴት ጓደኛህን ሄደህ ለመጎብኘት እንኳ ጊዜ አለህ። ለእግዚአብሔር ታዲያ ምነው ጊዜ አጣህ?"

አንዲህ ስል ቀጠልሁ "በእርግጥ ማድረግ የምትፈልገውን ከምርህ ካሰብህበት ትችላለህ።"

አንዳንድ ሰዎች አሥራታቸውን የማይከፍሉት ገንዘብ ስለሌላቸው እንደሆነ ይናገራሉ። በሌላ ነገር ላይ ግን ምን ያህል ገንዘባቸውን እንደሚያፈሱ ተመልከቱ። ችግሩ ገንዘብ ማጣት ሳይሆን የስግብግብነት መንፈስ እንደሆነ መረዳት ትችላላችሁ።

6. የሰዎችን ውሸት ለማሸነፍ *አናካዘን* ተጠቀም።

አንድ ጊዜ የሆነውን አስታውሳለሁ፤ ከአጥቢያ ቤተክርስቲያናት መጋቢያችን አንዱ የገንዘብ ማሰባሰብ ያደርግ ነበር።

በገንዘብ ማሰባሰቡ ወቅት መጋቢው ለቤተክርስቲያን የሙዚቃ መሣሪያዎች መግዣ የሚውል ገንዘብ ሰዎች እንዲሰጡ ማበረታታት ጀመረ።

የውጭ አገር ሰው የሆነ የአንዲት ሴት ባል ገንዘቡን ለመለገስ ተዘጋጀ። እጅንም ወደ ላይ ባወጣ ጊዜ እርሷ ካጠገቡ ሆና ወደ ታች ትጎትተው ነበር። ይህንን ድርጊቷን መጋቢው እንዳስተዋለ አላወቀችም።

አገልግሎቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ይህች ሴት ወደ መጋቢው ቀርባ እንዲህ አለች፤ "ታውቃለህ፣ በገንዘብ ማሰባሰቡ ወቅት ገንዘብ መስጠት ያልቻልነው ባሌ መስጠት ስላልፈለገ ነው።"

ቀጠለች፤ "መቼስ እነዚህ የውጭ አገር ሰዎችን ታውቃቸዋለህ፤ ቋጣሪዎች ናቸው።" አለች።

ያለችው ሁሉ ግን ውሸት ነበር። ምንም መስጠት ያልፈለገችው እርሷ ነበረች።

በመጨረሻም መጋቢውን እንዲህ አለችው፤ "እስቲ ማድረግ ያለብንን ነገር አያለሁ። እርግጠኛ ነኝ መለገስ የሚችል አቅም አለን።"

እኛ መጋቢዎች ሁሉ የምንመራውን ሕዝብ ሰበብና ውሸት እንዴት ማሸነፍ እንዳለበት ማወቅ ይኖርብናል።

7. *አናካዞን መንገድ ለማበጀት ተጠቀም።*

የተሳካለትን ሰው ካልተሳካለት የሚለየው ሰበቦችን አልፎ የመሄድ ብቃቱ ነው። በሉቃ 14 ላይ ያለውን ሰውዬ ልብ በል።

በተሰጡት ሰበቦችና ምክንያቶች አልተነዳም። ፈቃደኛ ባልሆኑት ተጋባዥ እንግዶች ሁሉ የተሰጠውን ሁኔታ መንገድ አበጀለት።

በአንድ ነገር አምናለሁ። አንድ ነገር በእርግጥ መሥራት የምትፈልግ ከሆነ መንገድን ታበጃለህ፤ ካልፈለግህ ግን ሰበቦችን ትደረድራለህ።

ወደ ግብጥ ወደ መጡ

ብዙ ወጣቶች ወደ ቤተክርስቲያን ለመምጣት ፈቃደኞች እንዳልነበሩ አስታውሳለሁ። እነዚህ ወጣቶች ሁሉ የተለያዩ ዓይነቶች ሰበቦች ነበሩዋቸው። በውስጤ የአናካዞ መንፈስ ሲነሣ እንዲህ አልሁ፤ "ወደ ቤተክርስቲያን መምጣት እነርሱ የማይፈልጉ ከሆነ ግብጥ እናዘጋጅላቸው።"

ለወጣቶቹ በከተማ ውስጥ በሚገኝ በአንድ ስፍራ ግብጥ አዘጋጀን። የግብጥ መጥሪያ ካርድ አዘጋጀንና ወደዚያ ጠራናቸው። በጣም ተደስተው ለራሳቸው እንዲህ አሉ "አንድ ሌላ መዝሙርናኛ አገኘን።"

በዚያ ምሽት የክርስቲያን መዚቃዎችን እየተጫወትን ከማያምኑት ጋር አብረን እንደጨፈርን አስታውሳለሁ። በኋላ ላይ ከመጡት ወጣቶች አንደኛው እንደውም በዚያ ቦታ ቢራ አለመቅረቡ አስገርሞት አጫውቶኛል። በግብዣው መሐል መዚቃውን ለስለስ ወዳለ ስልት ቀየርነውና ማስታወቂያ እንዳለን ገለጽን።

በዚያ ጊዜ እጅግ ልባቸው የጠነከረ የማያምኑ ወጣቶች ተቀምጠዋል። እኔም በፊታቸው ቆምሁና ወንጌልን ሰበኩላቸው። ነገሩ ግር ቢያሰኛቸውም ሕይወታቸውን ለጌታ ሰጡ። በዚያች ምሽት ብዙዎቹ ዳግም ልደትን አገኙ።

በአሁኑ ጊዜ በቤተክርስቲያን ውስጥ በዚያ አስገራሚ የወንጌል ስርጭት ምሽት ከዳኑት መካከል መጋቢያን የሆኑ አሉ። መጽሐፍ ቅዱስ በሚቻለው መጠን ሁሉ "ጥቂቶችን አድኑ" ይለናል።

አናካዞ ማለት ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር እንዲመጡ ማስገደድና መግፋት ማለት ነው። አናካዞ ሰው በማይመች ሁኔታዎች አይገደብም። እነዚህ ወጣቶች ቤተክርስቲያን መምጣት ያለመፈለጋቸው ሁኔታ አልያዘንም። ይልቁንም ለዚያ መንገድ አበጀንለት! መንገድ በሌለበት ሁኔታ ውስጥ መንገድን መቀየስ ተማር። ሰዎች በፊትህ የሚያስቀምጡትን ማናቸውንም ሰበቦች ማሸነፍን እወቅ።

8. *አናካዞን* ከተለመደው የወዳጆች ክበብ ውስጥ ለመውጣት ተጠቀምበት።

እያንዳንዱ ሰው የወዳጆች ቡድን አለው። የተለመደው በምታውቃቸውና በወዳጆች መካከል መቆየት ነው። ነገር ግን እግዚአብሔር በሕይወቱ እንዲጠቀም የሚፈልግ ሰው ከተለመደው የወዳጆች ክበብ ውስጥ ጥሶ መውጣትን ማወቅ አለበት። በዚህ ታሪክ ውስጥ የምናየው አናካዞው ሰው ከተለመደው የወዳጆች ክበብ ውስጥ ለመውጣት ሲገደድ እናያለን። ይህ እግዚአብሔርን ለማስደሰት ስንሻ የሚገጥመን እውነታ ነው።

የራሴ ክበብ ነበረኝ

በአክራ አብሬያቸው ያደግሁኝ የጓደኞች ማኅበር ነበረኝ። በዚያም የእውቅና የባለጸጎች ልጆች ነበርን። በልጅነቴ በአውሮፕላን ስበር በመጀመሪያ ማዕረግ ተቀምጬ አሕጉር አቀፍ ጉዞ ያደረግሁ ሲሆን ግንኙነቴም በከፍተኛ ደረጃ ላይ ከሚገኙ የማኅበረሰቡ ክፍሎች ጋር ነበር። ከአባቴ ጋር ዓለም አቀፍ በሆኑ ከተሞች ውስጥ ቆይታዬን አደርጋለሁ። መዝሙርናኛዎቼም ዋና፣ ፈረስ ግልቢያና የፈረስ ውድድሮች ነበሩ። በዚህ ዓይነት የቅንጦት ሕይወት የሚያሳልፉ ልጆች ታዲያ ጥቂቶች ናቸው።

በዚህ ክበብ ዙሪያ ታዲያ ምንም ያህል ክርስቲያኖች አልነበሩም። ዳግም ስወለድ ግን ከዚህ ክበብ ወጥቼ እጅግ ወደተለየ ክበብ ተቀላቅዬ ራሴን አገኘሁት። ከዚህ ቀደም ከማውቀው ወደተለየ የወዳጆች ክበብ መጣሁ።

እውነታው እግዚአብሔርን ደስ አሰኝ ዘንድ በእነዚያ በቀደሙት ክበቦች ውስጥ ብዙ ጊዜዬን ማሳለፍ አለመቻሌ ነው። በዚያ ክበብ ውስጥ ክርስቲያኖች የሉም። እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት ከወደድህ ከክበብህ እየወጣህ ሌሎች ቡድኖችን መቀላቀል ይኖርብሃል።

በዚህ ታሪክ ውስጥ የምናየው ባለጠጋ በጎዳናና በየአጥር ጥግ ከተቀመጡ ሰዎች ጋር በቀላሉ ጎብረትን መፍጠር የሚችል አይደለም።

በዚህ ታሪክ ላይ የምናየው ባለ ጸጋ ሰው ከሽባዎች፣ ከዓይነ-ስውራንና ከአካል ጉዳተኞች ጋር ጎብረትን የሚያደርግ አይደለም። ነገር ግን የቤተክርስቲያን እድገትን ለማምጣት የተለያየ ማኅበረሰባዊ ዳራ ካላቸው ሰዎች ጋር ጎብረትን መፍጠር ያስፈልጋል።

ትንሿ አስደሳች ጎብረት ማደግ ይኖርባታል

እንደማስታውሰው በ1984 በዩንቨርሲቲ ውስጥ የአንድ ጥሩ ጎብረት መሪ ነበርሁ።

እርስ በእርስ አጥብቀን እንዋደዳለን (እንዲያውም ሚስቴንም ያገኘኋት ከዚያ ነበር)። በዚያ ጎብረት ውስጥ የማውቃቸው ሰዎች እስካሁንም

ድረስ የቅርብ ጓደኞቼ ናቸው። ሆኖም ግን የእግዚአብሔር መንፈስ ከዚያ ትንሽ ጎብረት ወጥተን ወደማናውቃቸው እንድንሄድ ተናገረን።

አንዳንድ ሰዎች ይህችን ጎብረት በማስፋቱ ሐሳብ አለመስማማታቸውን ትዝ ይለኛል።

"ሌሎች ሰዎችን አምጥተን ከቀላቀልን፣ የሆነ የምናጣው ነገር ይኖራል" አሉ። "አነስተኛ ጎብረት መሆን ጠቃሚ ነው፣ ጥቂት መሆን ጥሩ ነው፣ ያው ልክ እንደ ጣፋጭ ትንሽ ቤተሰብ ማለት ነው" ይሉ ጀመር።

ነገር ግን ይህንን ጎብረት ለሌሎች በመድረስ ሂደት ውስጥ እንዲሳተፍ ገፋፋሁት። ወንጌል መስበክ አይደክመኝም ነበር። ሰዎች ኃጢአትን መሥራት አይሰለቹም። ታዲያ ለምንድነው ወንጌልን ከማሰራጨት የምትዝለው?

የሁለተኛ ዓመት የሕክምና ተማሪ ሳለሁ (በነገራችን ላይ አስቸጋሪ የሕክምና ትምህርት ዓመት ነው) ይህንን ቡድን በየቅዳሜው ማለዳ የወንጌል እወጃ እንዲያደርግ አንቀሳቀስሁት። ሁሉም ስለ እኛ ያውቅ ነበር። በማለዳ ጠርቶና ጎላ ብሎ ለሚሰማው ድምፃችን እውቅና ሰጥተውታል።

"እግዚአብሔር ሆይ ስለ ትንሿ ጎብረታችን አመሰግንሃልሁ፤ ሆኖም ግን ከዚህ ክበባችን ወጥተን ነፍሳትን መማረክ ይኖርብናል" እላለሁ። ከዚያች ትንሽ ክበብ መውጣት ግዴታችን ነበር።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ኢአማኒያን በስብከታችን ያን ያህል መመሰጥ አቆሙ። በአዲስ መንገድ ወይም አዲስ በሆነ የአናካዞ መንገድ እንደገና መነዳት ካልቻልህ መልእክትህ ግቡን አይመታም።

በየማለዳው መስበካችንን ስንቀጥል፣ ሰዎች ለስብከታችን ቁብ ሳይሰጡ ፊታቸውን አዙረው እንደሚተኙ ተገነዘብሁ። ለራሴ እንዲህ አልሁ "መልእክታችን ሰዎችን ወደ ጌታ እያመጣ አይደለም።"

የእግዚአብሔር መንፈስ ግን አንድ ብሩህ ሐሳብ ሰጠኝ።

በራቸውን አንኳኳ!

ሰዎች አሁን ድምፃችንን ስለሰመዱት አዲስ የሆነን ነገር ማድረግ ነበረብን። ለዚህም በየክፍላቸው በር ላይ እንዲቆሙ ቡድን ለመላክ ወሰንሁ።

በማለዳ ለሚሰብከውም ሰባኪ እንዲህ አልሁት "በስብከትህ መጨረሻ ሰዎች ጌታን እንዲቀበሉ ጥሪ ስታደርግ፣ በራቸውን ማንኳኳት እንጀምራለን።"

ለሚያደምጠህ ሰዎች "ክርስቶስን መቀበል የሚፈልጉ ከሆነ፣ በራቸው ሲንኳኳ እንዲሰሙና በራቸውንም መክፈት እንደሚኖርባቸው እኛም ገብተን ወደ ጌታ እንደምንመራቸው" እንዲነግራቸው አሳሰብሁት።

ሰባኪው መመሪያዬን ተከተለ። እነዚያ ቁብ ያልሰጡን ሰዎች አሁን በድንገት ትኩረታቸውን ወደ እኛ አደረጉ። ከማለዳው 11፡00 ሰዓት ላይ በራቸውን አንኳኳን! እመኑኝ፣ በእነዚያ ማለዳዎች የወንጌል እወጃ ብዙዎች በአስደናቂ ክብር ዳግም ተወለዱ።

ደኅንነት ለፈዘኞች

አንድ ወንድምን በተለይ አስታውሳለሁ። ክርስቲያኖች በልሳን በሚናገሩበት ጊዜ ያሾፍ ነበር። በልሳን ስጦታ ላይ ይቀልድ ነበር። ይህ እንግዲህ ውብ በሆነው በጋና ዩንቨርሲቲ ካምፓሶች ውስጥ ተሰራጭተው ካሉት ኩሬዎች የሚገኝ ሰካራምና ውሸታም ነው። በዚያ ማለዳ ወንጌላዊው ወዳጅ ከስበከቱ በኋላ እንዲህ አለ። "ምናልባት የበር መንኳኳት ድምፅ ትሰሙ ይሆናል፤ ዳግም ልደትን የምትሹ ከሆነ በራችሁን ክፈቱ የሆነ ሰው ይገባና ወደ ጌታ ይመራችኋል።" በአጋጣሚ የዚያን ሰው በር ያንኳኳሁት እኔው ነበርሁ።

በሩን ከፍቶ ወደ ውስጥ እንድንገባ ሲጋብዘን በጣም ተገረምሁ። እንዲህም አለ "ወደዚህ እንደምትመጣ አውቅ ነበር። ዛሬ የኔ ቀን ነው!" ከእርሱ ጋር ጸለይን። በዚያችም ማለዳ ልቡን ለጌታ ሰጠ። እስከዚህ ዕለትም ድረስ ይህ ሰው ጌታን ያገለግላል። በኃይል ቃሉን ለማወጅ በወጣንበት ጊዜ ዳግመኛ ልደትን ስላገኙት ሰዎች ሁሉ ለአምላኬ ክብር እሰጣለሁ። አናካዞ የሚሠራ ነው።

9. በቤተክርስቲያንህ ውስጥ አዳራሹ ጢም ብሎ እስኪሞላ ድረስ አናካዞን ተጠቀም።

. . . ገናም ስፍራ አለ አለው።

ሉቃስ 14፡ 22

አንድ የምወደው መዝሙርሙር እንዲህ ይላል። *መስቀሉ ጋር ላንተ ስፍራ አለ፣ መስቀሉ ጋር ላንተ ስፍራ አለ። ሚሊዮኖች ቢመጡም፣ አንድ ስፍራ አለ። መስቀሉ ጋር ላንተ ስፍራ አለ።*

በቤተክርስቲያንህ ውስጥ አንድ ትርፍ ስፍራ ኖሮ በእርካታ አትቀመጥ። በዚህ ታሪክ ውስጥ የምናየው ሰው አገልጋዮቹን የላከበት ምክንያት ስፍራ ስለነበር ነው።

እያንዳንዱ ቤተክርስቲያን ብዙውን ጊዜ ሊመጣ ከሚችለው ሰው በላይ ወንበሮችን ደርድሮ እንደሚያስቀምጥ አውቃለሁ። ባዶ ወንበሮች መጋቢውን ማነሣሣትና ቤቱ መመላት እንደሚገባው ማሳየት ይኖርበታል። የቤተክርስቲያን እድገት ዋና ግቡም በሰዎች የተሞላች ቤተክርስቲያንን መያዝ ነው።

ቤቴ እንዲሞላ . . . ዘንድ ግድ (አናካዞ) በላቸው።

ሉቃስ 14፡ 23

ወንጌል ስርጭት በቀጥታ ከቤተክርስቲያን እድገት ጋር ይያያዛል። ወደ ጌታ ሰዎችን ለመምራት የምናደርገው ጥረት ፍሬ ማፍራት ይኖርበታል። የቤተክርስቲያን ሕንፃዎቻችን በሰዎች መሞላት ይኖርባቸዋል። ምንም ዓይነት ነገር ይሁን፣ አገልጋይ ለአንድ ነፍስ መስቀሉ ጋር ስፍራ እንዳለ ማየት ይኖርበታል። ይህ አስተሳሰብ ካለን ደግሞ እግዚአብሔር ቤተክርስቲያንን ለመመላት ይጠቀምብናል።

በቤተክርስቲያኔ መጠን ረክቼ አላውቅም። አስር ሰዎች የነበርን ጊዜ፣ ሃያ እንድንሆን እፈልግ ነበር። ሃምሳ ስንሆን መቶ አልማለሁ። እግዚአብሔር መቶ ሰዎችን ሲሰጠኝ፣ "አምስት መቶ ሰዎች ቢኖሩ ምን ይመስል ይሆን?" እላለሁ። በቤተክርስቲያን ውስጥ በመቶ የሚቆጠሩ ሲሆኑ፣ "በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች ቢኖሩስ?" እላለሁ።

እንደሚመስለኝ ከጥቂት ጊዜ በኋላ አንድ መጋቢ ለጥቂት ምዕመኖቹ መስበክ ይሰለቸዋል። የሞላ ቤት እንዲኖረን መነሣሣት ይኖርብናል።

እነዚህ ቃላት በነፍሴ ውስጥ ይደውሉብኛል "ያ ቤቴ እንዲሞላ፣ ያ ቤቴ እንዲሞላ!" ውድ መጋቢ ሆይ፣ መስቀሉ ጋር አሁንም ስፍራ እንዳለ በጭራሽ አትዘንጋ።

ምዕራፍ 29

ሐናይዴያ እና ቢያዘ እንዴት የቤተክርስቲያንን እድገት እንደሚያመጡ

ሐናይዴያ እና ቢያዘ የቤተክርስቲያን እድገት ቁልፎች ናቸው። ወንጌል ስርጭት አዳዲስ ሰዎች በቤተክርስቲያንህ እንዲቀላቀሉ ማድረጊያ መንገድ ሲሆን ያለ ቢያዘ እና ሐናይዴያ ወንጌል ስርጭት ማድረግ አይቻልህም።

ቢያዘ

> እውነት እላችኋለሁ፥ ከሴቶች ከተወለዱት መካከል ከመጥምቁ ዮሐንስ የሚበልጥ አልተነሣም፤ በመንግሥተ ሰማያት ግን ከሁሉ የሚያንሰው ይበልጠዋል።
>
> ከመጥምቁም ከዮሐንስ ዘመን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ መንግሥተ ሰማያት ትገፋለች፥ ግፈኞችም ይናጠቋታል።
>
> ማቴዎስ 11፡11-12

ብዙ በክርስቶስ ያላመኑ ሰዎች ወደ ሲኦል ማጀት እየወረዱ ይገኛሉ። ይዘፍናሉ፣ ይጨፍራሉ፣ ይበላሉ፣ እንዲሁም ይጠጣሉ። ለምንሰብከውም ወንጌል ተቃውሞ ሲያሰሙ አይታዩም! ብዙዎቻችን ክርስቲያኖች

ኑሯችን በራሳችን ትንሽ ዓለም ዙሪያ ሲሆን ወደ ሲኦል እየወረዱ ስላሉትም ኃጢአተኞች ግንዛቤ ያለን አንመስልም።

በአንድ ወቅት ላይ በጋና ውስጥ ባለ ትልቅ ሆስፒታል ውስጥ ሬሳ ክፍል ተመድቤ እሠራ ነበር። አንድ ያስገረመኝን ነገር ላካፍላችሁ እወዳለሁ። በየደቂቃው መኪና ከሬሳ ክፍሉ ውጭ በር ላይ ይቆማል። በዚያ መኪና ውስጥ በኋላ መቀመጫ ላይ ወይም በመጫኛው ላይ የተጋደመ የሰው በድን ይኖራል።

በሬሳ ክፍሉ ደጅ ላይ እሆንና ሰዎች በቤት ውስጥ ወይም በመንገድ ላይ የሞቱባቸውን የሚወዷቸውን ወይም የዘመዶቻቸውን ሬሳ ይዘው ሲመጡ እመለከታለሁ። እነዚህ ሰዎች ከንዘናቸው በተጨማሪም

ይንቀጠቀጣሉ። መረዳት የሚያስፈልግህ ነገር ሰዎች ከጥቂት ሰዓታት በፊት ሲያነጋግሩት ከነበሩት አሁን ግን ጨርሶ ከተለያቸው ሰው ጋር መሆናቸውን ነው። የሚወዱትን ሰው በድን ወደ ማቀዝቀዣው ክፍል ያመጡታል።

ወደዚህ ሬሳ ክፍል የሚመጡ የሞቱ ሰዎች የተለየ ሰዓት ያላቸው አይመስልም። እዚያው ቆሜ ሳለሁ፣ ሰዎች በከተማው ውስጥ በየጊዜው እንደሚሞቱ እግዚአብሔር አመላከተኝ። ሞት በጠዋት ማለዳ ወይም ምሽት ሌሊት ብቻ እየለየ እንደማይመጣ መገንዘብ ያሻል። በየትኛውም ጊዜ የትኛውም ቦታ ሊከሰት ይችላል።

በሬሳ ክፍል በር ላይ ቆሞ የማያውቅ ሰው ሞት የተለመደና ተራ ነገር እንደሆነ መገንዘብ አይችልም። ሰዎች ለዘላለም እየተለዩ ይገኛሉ። ልክ ጌታ ነቢያቱ አንድ ነገር በሚያዩበት ጊዜ እንደተናገራቸው ለእኔም በዚያ የሬሳ ክፍል ደጃፍ ላይ ቆሜ ተናገረኝ። እንዲህ ሲል ጠየቀኝ፣ "ከእነዚህ ውስጥ ምን ያህሉ ሰው የዳነ ይመስልሃል?"

"ሞቼላቸዋለሁ፤ ሕይወቴን ለእነርሱ ሰጥቻለሁ፣ ግን ድነዋል?"

ክርስቲያን ወዳጄ ሆይ አድምጠኝ። የቤተክርስቲያን የጨረታ ጊዜዎቻችን፣ ሰርጎቻችን እንዲሁም ጎብረቶቻችንና ጥሩ የመዘምራን ቡድኖቻችን ይህንን ሁሉ ሕዝበ አዳም ወደ ክርስቶስ ለማምጣት በቂ አይደሉም። ብዙ ሕዝቦች ወደ ጥፋት እየተጣደፉ ይገኛሉ። ወደ ሲኦል እየወረዱ እንዳሉ እንኳ አያውቁም።

የሙዚቃ ድምፅ ሰሙ

ይህ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ እስረኞች ወደ ማጎሪያ ካምፕ ሲወሰዱ የነበረውን ሁኔታ ያስታውሰኛል። ልብሳቸውን ከተገፈፉና ራቁታቸውን ከሆኑ በኋላ የመርዝ ጋዝ ወዳሉባቸው ክፍሎች ይጋዛሉ።

እነዚያ ክፍሎች ውስጥ ተጠናቀው ከገቡ በኋላ አሳሪዎቻቸው ለእስረኞቻቸው ያማረ ጥሩ ሙዚቃ ይጫወቱላቸዋል። እነርሱም ሙዚቃውን ይሰማሉ። እንዴት አስደሳችና የሚያነቃቃ ሙዚቃ ይሰሙ መሰላችሁ! "በእርግጥ ምንም ክፉ ነገር አይሆንብንም"

በማለት ያስባሉ። ነገር ግን በመቀጠል ሙዚቃ በተጫወቱላቸው በእነዚያ ሰዎች እጅ እንደሚገደሉ ብዙዎቹ አያውቁም ነበር።

ዛሬም የማያምኑቱ ዕጣ ይኸው ነው። የዲያብሎስን ሙዚቃ ይሰማሉ። የዚህን ዓለም የሚዚቃ ቃናና እሹሩሩ በማዳመጥ ይዝናናሉ። በዚህም ምክንያት ወደ ጥፋታቸው እየፈጠኑ መሆኑን ይዘነጋሉ። ". . . በሬ ለመታረድ እንዲነዳ. . ."(ምሳ. 7፡22)

በማቴ 11፡ 12 መጽሐፍ ቅዱስ ግፈኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት በኃይል ይወስዷታል ይላል። ይህ ታዲያ ምን ማለት ነው?

የሃያኛው ክፍለ ዘመን አዲስ ኪዳን እንዲህ አርጎ ያስቀምጠዋል፣ . . .ሰዎች ኃይልን ተጠቅመው ይይዟታል. . .

የዊሊያም ትርጉም ደግሞ፣ . . . ሰዎች እንደ ውድ ሽልማት ይይዟታል. . .ይላል።

ጉድ ስፒድ የተባለው ትርጉም ደግሞ፣ . . . ሰዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት በዐውሎ ነፋስ ጉልበት ይነጥቋታል. . .

የወይማውዝ ትርጉም በሌላ በኩል፣ . . . የእግዚአብሔር መንግሥት የግፈኞችን ጥቃት ትቋቋማለች. . .በማለት ይገልጻል።

እነዚህ ሁሉ ትርጉሞች አንድ ነገር ይናገራሉ። ለስላሳ ቃላት፣ ጥሩ ዝማሬዎች፣ ስንኩል ስብከቶችና የተረጋጋ የመዘምራን ቡድን ለዚህ ቸልተኛና ምንም ለማይመስለው ዓለም ያን ያህል ፋይዳ የላቸውም። ብዙዎች ማወቅ አይፈልጉም። ስለዚህም ተታልለዋል።

የቤተክርስቲያን ጨዋታዎችም አይጠቅሙም

ለእነርሱ ኢየሱስ ዛሬ ይምጣ ነገ ግዳቸው አይደለም። "እኔን ተወኝ ወደዚያ፣" ይሏችኋል። "ይህ የቤተክርስቲያን ጉዳይ የሚመለከተው አንተን ነው "

መጽሐፍ ቅዱስ ቢያዞ ብሎ የሚጠራው ተግባር የሚያስፈልገው ለዚህ ነው። ቢያዞ ማለት ኃይልን መጠቀም ወይም ማስገደድ ማለት ነው። ብዙ ሰዎች በዲያብሎስ ታውረዋል። መንግሥተ ሰማይና ሲኦል ለሚባሉት እውነታዎች ዓይናቸውን መግለጥ ይኖርብናል።

የዚህ ዓለም አምላክ . . . አሳብ አሳወረ

2ኛ ቆሮንቶስ 4፡4

የሐዋርያው ጳውሎስ ሥራ ጥሩ ስብከቶችን ማቅረብ ብቻ አልነበረም፤ የሰዎችን ሐሳብ ማስለወጥና የማያምኑትን ዓይን መክፈትም ሥራው ነበር።

ሁልጊዜም ሰዎች የሆነ መልእክት ቸል ሲሉ አውቃለሁ። ሆኖም ግን ይህንን ዋናና አስፈላጊ መልእክት ቸል እንዲሉት አልፈቅድም። አንድ ማለዳ ላይ አንድ ቡድን ውስጥ ያለነው የዩንቨርሲቲ ወዳጆቼ በአዳራሽ ውስጥ ስንሰብክ ራሳችንን አገኘነው።

ከተማ አቀፍ የጆማ ስብከት ሲኖረንም መድረክ ላይ እቆምና ለቤተክርስቲያን አባላቶቼ ወደ ማጎበረሰቡ ውስጥ እንዲዘልቁ አሳስባቸዋለሁ። ወደ እኛ እስኪመጡ ድረስ አንጠብቃቸውም። ቤታቸው ድረስ ሄደን እናመጣቸዋለን።

አንድ ቀን እንዲያውም ሴተኛ አዳሪዎች በብዛት ወደሚገኙበት ገብተን ወደ ጆማው ስብከት ይዘን መጥተናል። እነዚህ ሴተኛ አዳሪዎች በኋላ ላይ ከመድረክ ላይ ጥሪ ሲደረግላቸውና ሕይወታቸውንም ለጌታ ሲሰጡ እጅግ ተደሰትሁ። በእርግጥ እነዚህን ሴተኛ አዳሪዎች "ከሥራ ቦታቸው" ግድ ብለን ባናመጣቸው ኖሮ ደኅንነትን አያገኙም ነበር። ብዙዎች ሴተኛ አዳሪዎች ወደ ቤተክርስቲያን አይሄዱም። በተለመደው የየዕለት የኑሮ ዐውዳቸው ውስጥ በመሸከርከር በቀጠሉ ነበር። እኛም ለራሳችን ብቻ ሰብከን እናበቃ ነበር።

ክርስቲያን ወዳጆቼ ሆይ፣ ጨዋታ እናቁም። ወንጌል የምንሰብክ ከሆነ ለራሳችን አይሁን። እንውጣና (በአናካዞ እና በቢያዞ መንፈስ) ወደ ጌታ እንዲመጡ ግድ እንበላቸው።

አናይዴያ

እላችኋለሁ፥ ወዳጅ ስለ ሆነ ተነሥቶ ባይሰጠው እንኳ፥ ስለ ንዝነዛው (አናይዴያ) ተነስቶ የሚፈልገውን ሁሉ ይሰጠዋል።

ሉቃስ 11፡8

በሉቃ 11 ኢየሱስ ሦስት እንጀራ ስለፈለገው ሰው ታሪክ ይነግረናል። ይህ ሰው ዓይኑን በጨው የታጠበ እፍረት የሌለው ሰው ነበር።

ከዚያም በአጉል ሰዓት ወደ ወዳጁ ቤት ሄደ። የቤቱም ባለቤት ተነሣ።

ምናልባት እንዲህ ብሎ ጮኾበት ይሆናል፣ "ምንድነው? በዚህ አካባቢ የታጠቁ ወንበዴዎች አሉ? እሳት ተነሥቷል? ምንድነው ውጪ እየሆነ ያለው?" ምናልባት ደግሞ አገልጋዩ "አይ ጎረቤቱ ነው፣ለእንግዶቹ ጥቂት እንጀራ ፈልጎ ነው" ብሎ ይሆናል።

ውድ ክርስቲያን ወዳጄ ሆይ፣ ብዙዎቻችን በእኩለ ሌሊት ወዳጆቻችንን አንረብሽም። በተለይ ደግሞ ቁራሽ እንጀራ ለመውሰድ በዚያ ዓይነት ሰዓት መሄድ የማይታሰብ ነገር ነው!

የኢየሱስ መልእክት እዚህ ጋር ቀላልና ግልጽ ነው። አንዳንድ ነገሮችን ለመከወን ሐፍረት የሚሰማህ ከሆነ ልታሳካ አይቻልህም። ነገር ግን የቤተክርስቲያን እድገትን ለማሳካት ሐፍረት የማይሰማህ ከሆነ ብዙዎች ያለሙትን አንተ ማሳካት ይቻልሃል! በሕዝብ ዘንድ ላላቸው ገጽታ ብዙ የሚጨነቁ ሰዎች ለእግዚአብሔር ብዙ መሥራት እንዲሁም ማሳካት እንደማይችሉ ጌታ አመላክቶኛል።

የቤተክርስቲያን እድገትን ሐሳብ መከተል ያሳፍርሃልን?

ቤተክርስቲያንን ለመትከል ሐፍረተ ቢስ መሆንን ይጠይቃል። ለጓደኛዬ ቤተክርስቲያን የመትከል ሐሳብ በነገርሁት ጊዜ በአግራሞት ተመለከተኝና እንዲህ አለኝ፣ "ለመሆኑ ሰዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን ባይመጡስ? ሐፍረት ላይ እኮ እንወድቃለን። በከተማው ውስጥ ያሉ ሰዎች ቤተክርስቲያንን ለመትከል ሞክረው አልተሳካላቸውም" ይሉናል።

ቤተክርስቲያንን መትከል የአንድ የአገልግሎትን ክፍል ገንጥሎ መሄድ ማለት አይደለም። እኔ ግን ሳወራ የነበረው ሁለትና ሦስት ሰዎች ወዳሉበት ክፍል ውስጥ መግባት ብሎም ለእነርሱ መስበክ ነበር። ለእነዚህ ጥቂት ሰዎች ታዲያ በታላቅ ቤተክርስቲያን ውስጥ እንዳሉ መንገር ሐፍረተ ቢስ መሆን ይጠይቃል።

በባዶ ክፍል ውስጥ መቆምን፣ በሐፍረትና በመናቅ ውስጥ ለማለፍ ያልቆረጥህ ከሆነ ትልቅ ነገር ለእግዚአብሔር ማድረግ አትችልም።

የቤተክርስቲያን ሥራ ያሳፍርሃልን?

አንድ መጋቢ በመድረክ ላይ ቆሞ የአዲስ ነፍሳት ጥሪ (ሰዎች ሕይወታቸውን ለክርስቶስ እንዲሰጡ) ማድረግ እንደሚያስፈራው ነግሮኛል። አንድም ሰው ምላሽ ባይሰጥስ?

ይህ አያሳፍርህም? ሰዎች የተቀባህ እንዳልሆንህ ከመቁጠራቸውም በላይ መልእክትህ ብርቱ እንዳልሆነ ያስባሉ። እንግዲህ ሰዎችን ኃይለኛ ከሆነው አገልግሎታቸው የሚገድባቸው ብዙ የለመዱት ሐሳባቸው ነው።

ከዕለታት አንድ ቀን ከቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች አንዷ ጠራችኝና አንድ ሰው ለመጀመሪያ ጊዜ ለአዲስ ልደት ጥሪ ምላሽ እንደሰጠ ነገረችኝ። ይህቺ ሴት ምንም እንኳ ማንም ለጥሪዋ ለረጅም ጊዜ ምላሽ ባይሰጥም፣ በአናይዴያ (ያለ ሐፍረት በጽናት) በስተመጨረሻ ምላሽ አግኝታለች!

በፊውስ አገልግሎት ሐፍረት ይሰማሃልን?

ቁራሽ እንጀራ የጠየቀው ሐፍረተ ቢስ ሰውዬ በመጨረሻ ግቡን አሳክቷል። ለመጀመሪያ ጊዜ እንዴት ለታመመ ሰው እንደጸለይሁ አስታውሳለሁ። ሰዎች ስለ እኔ ምን እንደሚያስቡ በማሰብ ተጨንቄ ነበር።

ብዙ ጊዜ በመድረክ ላይ በምቆምበት ጊዜ ዲያብሎስ እንዲህ ይለኛል "ለምስክርነት ማንንም ባትጠራ ይሻልሃል፣ ማንም አልተፈወሰም።"

በመቀጠልም "ራስህን ከዚህ በላይ አታዋርድ። አገልግሎትህን እዚህ ጋር አቁምና ሕዝቡን ወደ ቤቱ ሸኘው።"

የእግዚአብሔር መንፈስ ግን በውስጤ ይነሣና ለራሴ እንዲህ እላለሁ፣ "አላፍርም። ዛሬ አንድም ሰው እንኳ ባይፈወስ፣ ደግሜ ደጋግሜ አደርገዋለሁ! አንድ ቀን አንድ ሰው ይፈወስ ይሆናል።" አሁን ብዙ ሰዎች መፈወሳቸውን ስናገር ደስታ ይሰማኛል።

ከሕክምና ት/ቤት ከተመርቅሁ በኋላ የሕክምና ዶክተር ሆኜ የሠራሁት ለአንድ ዓመት ብቻ ነው።

በሙሉ ጊዜ አገልግሎት ታፍራለህን?

ጌታ በሙሉ ጊዜ አገልግሎት ውስጥ እንድሰማራ በተናገረኝ ጊዜ እንዲህ ብዬ ተከራከርሁ። "እየሠራሁ በቂ ገንዘብ ወደ ቤተክርስቲያን ባመጣ ይሻላል።

"ሰዎችስ ምን ይሉኛል? አንዲህ ዓይነት የተከበረ ሙያ ትቼ አከራካሪ ወደ ሆነ ሥራ ውስጥ ስገባ" ጌታን እንዲህ አልሁት፣ "ቤተክርስቲያኔን ማንም አያውቅም! እኔንም የሚያውቅ የለም!

"ከሁሉ የከፋው ደግሞ በሰዎች መባና ስጦታ ሕይወትን መኖር ለእኔ አሳፋሪ መሆኑ ነው።

"ይህ አሳዛኝ ሕይወት ነው! ሰዎች ለእኔ ኑሮ ሲባል ገንዘባቸውን ማዋጣት አለባቸውን? ክብርን ዝቅ የሚያደርግ ነው" ብዬ አሰብሁ።

ሆኖም ግን ጌታ እንዲህ ሲል ተናገረኝ፣ "ወንጌልን የሚሰብክ፣ ከወንጌል ሊጠቀሙ ይገባል።"

> እንዲሁ ደግሞ ወንጌልን የሚሰብኩ ከወንጌል ቀለብ እንዲቀበሉ ጌታ ደንግጎአል።
>
> ፩ኛ ቆሮንቶስ 9፡14

እንደ ዶክተር ያለኝን ክብር መቅበርና ያለ ሐፍረት ወደ ሙሉ ጊዜ አገልግሎት መግባት ነበረብኝ። ሐፍረትን መጣል (አናይዴያ) በሚለው መገለጥ አማካኝነት በአገልግሎት ገፍቼ ሄድሁ። ማንም ከእኔ ይወጣሉ ብሎ የማይገምታቸውን ነገሮች አከናወንሁ።

አናይዴያ (ሐፍረትን መጣል) ለእግዚአብሔር ታላላቅ ነገሮችን የምትከውንበት ቁልፍ ነው።

ክፍል 12

የቤተክርስቲያን እድገትና ጠንካራ አመራር

ምዕራፍ 30

የቤተክርስቲያንን እድገትን እንድታሳካ ለምን ጠንካራ መሪ መሆን እንደሚገባህ

. . ይሆን ቃሌን ሰምቶ የሚያደርገው ሁሉ ቤቱን በዓለት ላይ የሠራ ልባም ሰውን ይመስላል።

ማቴዎስ 7፡24

ስለ መጋቢ የተለመደው አስተሳሰብ መጋቢ ማለት ለስላሳ፣ ሩኅሩኅና ሌላውን መረዳት የሚችል ሲሆን የምእመኑን ችግር አንድ በአንድ የሚያዳምጥ ማለት ነው። እንዲህ ዓይነቱ ሩኅሩኅ መጋቢ የሚቀርቡትን ሐሳቦች ሁሉ የሚረዳና ተወዳጅ ነው። ለእያንዳንዱ ሰው ጊዜ ያለው ሲሆን ለሁሉም ሕፃናትም እንክብካቤን ይሰጣል። ተግባቢና የዋህ ሲሆን ሁሉም ሰው ሊያወራው የሚፈልገው ዓይነት ሰው ነው።

እኔም በአእምሮዬ የሣልሁት መጋቢ እንዲህ ዓይነት ነበር። ሆኖም ግን በዶክተር ዴቪድ ያንግ ቾ (በዓለም ላይ የትልቁ ቤተክርስቲያን መጋቢ) በሆኑት ሰው ታላቅ ቤተክርስቲያንን ለመገንባት እጅግ ጠንካራ መሪ መሆን እንደሚያስፈልግ ሲነገር ደንግጫለሁ።

ምክንያቱም መጋቢ ለስላሳ፣ የዋህ፣ ተንከባካቢና ሕዝቡን በጌታ ፍቅር የሚወድ ነው ከሚለው ትንታኔ ጋር የሚጋጭ ሐሳብ ሆኖ ስለታየኝ ነው።

ለመሆኑ የአመራር ጥንካሬና ብርታት ብዙ ሰዎችን በአረኝነት ከመመገብ ጋር የሚያያይዘው ምንድን ነው? ጊዜ ባለፈ ቁጥር የቤተክርስቲያን እድገት የሚፈልግ ሰው እንዴት ዓይነት ብርቱና ጠንካራ የመሆን አስፈላጊነትን ተገንዝቤያለሁ።

በእርግጥም የዚህ ጠንካራ መሪነት ለቤተክርስቲያን እድገት አስፈላጊነት ሙሉ ለሙሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሐሳብ መሆኑን የእግዚአብሔር ቃል ይደግፈዋል።

1. *ታላቅን ቤት በዓለት መሠረት ላይ ለመመሥረት ጠንካራ መሪ መሆን ግድ ነው።*

ታላቅ ቤተክርስቲያንን በለስላሳ መሪ መገንባት አይቻልም። ግዙፍ አገልግሎት የሚቋቋመው በጠንካራ መሪ ላይ ነው። ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔር ቤት ስትሆን ዓለት የሆነ መሠረትም ያስፈልጋታል።

ዓለት የሚያስፈልግበት ምክንያት በተተከለችው ቤተክርስቲያን ላይ ዝናቡ ስለሚዘንብ፣ ጎርፍ ስለሚመጣ፣ ነፋሱም ስለሚነፍስ ነው። መሠረቱ ላይ ጥንካሬ ከሌላ ለወደፊቱ ምንም ዓይነት ተስፋ አይኖርም።

> . . . ይህን ቃሌን ሰምቶ የሚያደርገው ሁሉ ቤቱን በዓለት ላይ የሠራ ልባም ሰውን ይመስላል።
>
> ዝናብም ወረደ ጎርፍም መጣ ነፋሱም ነፈሰ ያንም ቤት ገፋው፥ በዓለት ላይም ስለ ተመሠረተ አልወደቀም።
>
> ማቴዎስ 7፡24-25

2. *ጠንካራ መሪ መሆን አለብህ። ምክንያቱም ክርስቶስ ራሱ የቤተክርስቲያን አዕማድ የሆነውን ጴጥሮስን ጠንካራ ዓለት እንዲሆን ፈልጓል።*

የጴጥሮስን ስም "ዓለት" በማለት ቀየረው። ምክንያቱም አለማቀፋዊ የሆነች ቤተክርስቲያን ለመመሥረት ጠንካራ ሰው እንደሚያስፈልግ ያውቃል። ኢየሱስ ጴጥሮስ በቀላሉ የማይናወጥ ጠንካራ መሪ እንዲሆን ፈልጓል። አንተም በዙሪያህ በሚሆነው የማትናወጥ ጠንካራ መሪ መሆን ይኖርብሃል።

> እኔም አልሃለሁ፥ አንተ ጴጥሮስ ነህ፥ በዚችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፥ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም።
>
> ማቴዎስ 16፡18

3. *ጠንካራ መሪ መሆን አለብህ፤ ምክንያቱም ኢየሱስ ታላቁን ነቢይ ዮሐንስን ጠንካራ እንዲሆን ተናግሯልና።*

ለስላሳና የሚዋልሉ ዓይነት ሰዎች ታላላቅ አገልግሎቶችን መምራት አይቻላቸውም። የሚዋልል ሰው የመወሰን ችግር ያለበት መሪ ነው። ብርታትም ሆነ ገንቢ ባሕርይ አይኖረውም። ታላላቅ አገልግሎቶች

ብዙውን ጊዜ ይመሩ የነበሩት በታላላቅ መሪዎች ሲሆን፣ እነርሱም ሰዎች በሚሉት ነገር ሳይናወጡ በእግዚአብሔር ሐሳብ የሚንቀሳቀሱ ናቸው።

እነዚያም ሲሄዱ ኢየሱስ ለሕዝቡ ስለ ዮሐንስ ሊናገር ጀመረ እንዲህም አለ፦ ምን ልታዩ ወደ ምድረ በዳ ወጣችሁ?

ነፋስ የሚወዘውዘውን ሸምበቆን? ወይስ ምን ልታዩ ወጣችሁ? ቀጭን ልብስ የለበሰ ሰውን? እነሆ፥ ቀጭን ልብስ የለበሱ በነገሥታት ቤት አሉ።

ወይስ ምን ልታዩ ወጣችሁ? ነቢይን? አዎን እላችኋለሁ፥ ከነቢይም የሚበልጠውን።
ማቴዎስ ፲፩፥7-9

4. ሁሉ ነገር በመሪ ላይ የተወሰነ ስለሆነ ጠንካራ መሪ መሆን ይኖርብሃል።

. . . እረኛውን እመታለሁ የመንጋውም በጎች ይበተናሉ።
ማቴዎስ 26፡31

ሁሉ ነገር በእረኛው ይወሰናል። ሁሉ ነገር በመሪው ይወሰናል። እረኛው ወደ ታች ከወረደ እያንዳንዱ ይወርዳል። መላው ማኅበር ለስላሳ፣ ደካማና በሚዋልል መሪ ላይ ሊደገፍ አይችልም። የመርከብ ካፒቴን ወይንም የአውሮፕላን አብራሪ መሆን ማለት የእያንዳንዱ ሕይወት በአንተ እጅ ላይ ነው ማለት ነው።

ለስላሳው አብራሪ

አንድ ጊዜ ከኮሎምቢያ ወደ ኒው ዮርክ አውሮፕላን በሚያበር ደካማ መሪ ላይ የተሠራ ጥናታዊ ፊልም ተመልክቻለሁ። በአየር ማረፊያው በነበረው የትራፊክ መጨናነቅ ምክንያት የማሳረፊያ ጊዜውን እንዲያዘገየው ተነገረው። የማይታመነው ነገር ግን በአውሮፕላን ውስጥ የነበረውን ነዳጅ በጠቅላላ እስኪጨርስ፣ አውሮፕላኗም እስክትከሰከስና ብዙ ሰዎች እስኪያልቁ ድረስ በዚያ አየር ዙሪያ ማብረሩን ቀጥሎ ነበር።

በዚህ አሳዛኝ ክስተት ዙሪያ ምርመራ ተካሄዶ ነበር። በውጤቱም ይህ አብራሪ ነዳጁ እስኪያልቅበት ድረስ አለማስተዋሉ ታወቀ።

በዚያ ምሽት ይህ ደካማ የሆነ አብራሪ ራሱን ጨምሮ ብዙ ሰዎችን የገደለ ሲሆን ምክንያቱ ደግሞ የአየር ትራፊኩን ተቆጣጥሮ በተገቢው ጊዜ በፍጥነት አውሮፕላኑን ማሳረፍ ባለመቻሉ ነው።

በተጨማሪም ተሳፋሪው ሁሉ በሞት አደጋ ላይ መሆኑን ባወቀበት ጊዜ በአስገዳጅ ሁኔታ (ቢያስፈልግ በሕገ ወጥ መልኩም) አውሮፕላኑን ለማሳርፍ የሚያበቃ ኃይል አጥሮት ነበር።

እንግዲህ ደካማንና ለስላሳን ሰው ለሁሉም ነገር ኃላፊ አድርጎ መሾም ችግሩ እዚህ ላይ ነው። ለዚህ ነው ኢየሱስ ጴጥሮስ ዓለት እንዲሆን የፈለገው። የቤተክርስቲያን የበላይ ጠባቂ እንዲሆን የሚፈልገው ሰው ጠንካራ ሰውን ነው።

5. ጠንካራ መሪ መሆን አለብህ፤ ምክንያቱም የቤተክርስቲያን ራስ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ጠንካራ መሪ ሲሆን ለዚያም አይጸጸትም።

> አንድ መክሊትም የተቀበለው ደግሞ ቀርቦ፦ ጌታ ሆይ፥ ካልዘራህባት የምታጭድ ካልበተንህባትም የምትሰበስብ ጨካኝ ሰው መሆንህን አውቃለሁ፤
>
> ፈራሁም ሄጄም መክሊትህን በምድር ቀበርኋት። እነሆ፥ መክሊትህ አለ።
>
> ጌታውም መልሶ እንዲህ አለው፦ አንተ ክፉና ሃኬተኛ ባሪያ፥ ካልዘራሁባት እንዳጭድ ካልበተንሁባትም እንድሰበስብ ታውቃለህን?
>
> ስለዚህ ጥንዚቤን ለለዋጮች አደራ ልትሰጠው በተገባህ ነበር፥ እኔም መጥቼ ያለኝን ከትርፉ ጋር እወስደው ነበር።
>
> ማቴዎስ 25፡24-27

ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ የመሪን ጠንካራ መሆን አስፈላጊነት በምሳሌዎቹ ያብራራላቸዋል። ለዚህ እውነታም ምንም ዓይነት ይቅርታ ሲጠይቅ አናይም። በዚህ ምሳሌ ውስጥ አገልጋዩ መሪው ጠንካራ መሆኑን ሲገልጽ "..ጨካኝ ሰው መሆንህን.." ገልያታል። በዚህ አገልጋይ አስተያየት ጌታው (መሪው) የማይገባውን ጥቅም ወስዷል። ጌታም ጠንካራ ሰው መሆኑን አልካደም፤ እንዲያውም ያልዘራውን እንደሚያጭድ ጨካኝ ተመስሏል።

ወዳጄ ሆይ፣ በመንግሥቱ ውስጥ አንድ ነገር አስተዋጽኦ ማድረግ ከፈለግህ እንደ ጌታ ጠንካራ መሆን ይፈለግብሃል።

ምዕራፍ 31

የታላቅ ቤተክርስቲያን መጋቢ ጥንካሬና ውሳኔዎች

የአንድ ታላቅ ቤተክርስቲያን ጥንካሬና ውሳኔ ሰጭነት የአመራር ባሕርይውን ይወስናል። የታላቅ ቤተክርስቲያን መጋቢ ሕዝቡን ወደ ተስፋይቱ ምድር ወደ ፊት ለማስገባት ጉልበት ሊኖረው ይገባል።

ጉልበትና አቅሙ የሚታየውም በጠንካራ ውሳኔዎቹና በውሳኔው መሠረት የሚንቀሳቀስ መሪ እንደሆነ ነው።

አንድ ጠንካራና ብርቱ መጋቢ ታላቅ ቤተክርስቲያንን ለመገንባት የሚወስዳቸውን ጥቂት ውሳኔዎች ከዚህ በመቀጠል ላካፍልህ እወዳለሁ።

1. ታላቅ ቤተክርስቲያንን የሚገነባ መጋቢ በትክክለኛ ቦታ ትክክለኛ ሰዎችን ለማስቀመጥ ውሳኔ ማስተላለፍ አለበት።

ብዙኃኑ በሚያስበው መንገድ የምትጓዝ ከሆነ የትልቅ ቤተክርስቲያን መጋቢ ልትሆን አትችልም። ዮሴፍ የጠቅላይ ሚኒስትርነት ሥልጣን ከመያዙም በላይ በመላው ግብፅ ላይ የበላይ ነበር።

ሌሎች የግብፅ የመምሪያ ኃላፊዎች አንድ እስራኤላዊ ባሪያ አለቃቸው ሲሆን ሲያዩ ምን ሊሰማቸው እንደሚችል መገመት ትችላለህ?

ፈርዖንም ዮሴፍን አለው። እንደ አንተ ያለ ብልህ አዋቂም ሰው የለም፥ እግዚአብሔር ይህን ሁሉ ገልጦልሃልና።

አንተ በቤቴ ላይ ተሾም፥ ሕዝቤም ሁሉ ለቃልህ ይታዘዝ እኔ በዙፋኔ ብቻ ከአንተ እበልጣለሁ።

ፈርዖንም ዮሴፍን፦ በግብፅ ምድር ሁሉ ላይ ሾምሁህ አለው።

ዘፍጥረት. 41፡39-41

2. ታላቅ ቤተክርስቲያንን የሚገነባ መጋቢ ከሥርዓት ውጭ የሚሆኑትን መገሠጽ ይኖርበታል።

ከሥርዓት ውጪ የሚሆኑትን መገሠጽ የማትችል ከሆነ የታላቅ ቤተክርስቲያን መጋቢ ልትሆን አትችልም። ሰዎች በቋሚነት ከሥርዓት ውጪ ይሆናሉ። በዚያም ምን ያህል ጠንካራ መሆንህን ያያሉ። ምን ያህል ርቀት መሄድ እንደሚችሉ ማወቅ ይፈልጋሉ። ምኞት የማይሰጡ ሁኔታዎችን ለመጋፈጥ ብቁ መሆን አለመሆንህን ይፈትናሉ። ሁሉም ምን ያህል ጠንካራ መሆንህን ለማወቅ ይመለከትሃል።

> እርሱ ግን ዘወር ብሎ ጴጥሮስን። ወደ ኋላዬ ሂድ፥ አንተ ሰይጣን፤ የሰውን እንጂ የእግዚአብሔርን አታስብምና ዕንቅፋት ሆነህብኛል አለው።
>
> ማቴዎስ 16፡23

3. ታላቅ ቤተክርስቲያንን የሚገነባ መጋቢ ጠንካራ ውሳኔዎችን ማሳለፍ የሚችል ሲሆን በአገልግሎት ውስጥ ሚስቱ እንድትመራው መፍቀድ አይኖርበትም።

አዳም በሚስቱ ተነድቶ ዓለማችን አሁን ላለችበት መከራ ዳርጓታል። አብርሃም በሚስቱ ተመርቶ እስማኤልን ወልዷል።

በሁለቱም ሁኔታዎች ላይ መጽሐፍ ቅዱስ፣ "አዳም/አብርሃም የሚስቱን ቃል ሰማ. . .ይላል። አክአብ በሚስቱ ተነድቶ የነፍስ ግድያና ዘረፋ ፈጽሟል።

አክአብ ልክ እንደ አዳምና አብርሃም በሚስቱ ተነድቶ ክፋትን ለማድረግ ራሱን አሳልፎ ሰጥቷል።

በሌላ በኩል ግን ኢዮብ እግዚአብሔርን እንዲረግም በሚስቱ ጫና ቢደረግበትም ምንም ክፉ ነገር ከአፉ አልወጣም። እንዲያውም ሚስቱን ሰነፍ ሴት! የሚል ስያሜ ሰጥቷታል። ከሚስትህ በኩል የሚመጣውን አሳች ተጽዕኖ መቃወም ካልቻልህ የታላቅ ቤተክርስቲያን መጋቢ ልትሆን አትችልም።

ጠንካራ የታላቅ ቤተክርስቲያን መጋቢ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ሁሉ ስንፍናን በሚስቱ ውስጥ መለየት ይገባዋል። ሚስትህ መልዓክም አምላክም አይደለችም። እንደ ማንኛውም ሰው ነች። እናም ክፉውን

ከበጎው መለየት ካልቻልህ የታላቅ ቤተክርስቲያን መጋቢ ልትሆን አትችልም።

ሚስትህ ምናልባትም እግዚአብሔርን ስደብና ሙት ብትልህ ሰነፍ ሴት ብለህ ልትጠራት አቅም ሊኖርህ ይገባል።

ሚስቱም። እስከ አሁን ፍጹምነትህን ይዘሃልን? እግዚአብሔርን ስደብና ሙት አለችው።

> እርሱ ግን አንቺ ከሰነፎች ሴቶች እንደ አንዲቱ ተናገርሽ ከእግዚአብሔር እጅ መልካሙን ተቀበልን፥ ክፉ ነገርስ አንቀበልምን? አላት። በዚህ ሁሉ ኢዮብ በከንፈሩ አልበደለም።
>
> ኢዩኤል 2፡9-10

4. ታላቅ ቤተክርስቲያንን የሚገነባ መጋቢ ሚስቱ በስፍራዋ እንድትቀመጥ ጠንካራ ውሳኔዎችን ያደርጋል።

የታላቅ ቤተክርስቲያን መጋቢ ሚስቱ የእግዚአብሔርን ሥራ እንዳታፈርስበት ማረጋገጥ ይኖርበታል። የሚልኮል አስተያየት የዳዊትን የምስጋናና የአምልኮ አገልግሎት ሊያስተጓጉል ይችል ነበር። ዳዊት ግን ያንን አልፈቀደም። ሚስቱ ካሰበችው ውጪ የምስጋናና የአምልኮ አገልግሎቱን ቀጠለ። ተገቢ የሆነ ተግሣጽ ለእርሷ ከመስጠቱም በላይ ከእርሷ ራሱን ጠበቀ! ይልቁንም "የተተወውን የምስጋናና አምልኮ" አገልግሎት ቀጠለ።

ዛሬ የምንዘምራቸው እነዚያ ዝማሬዎች የፈለቁት ከዚያ ራሱን ፈጽሞ ለእግዚአብሔር ከተወ ሰው ልብ ውስጥ ነው።

> ዳዊትም ቤተ ሰቡን ሊመርቅ ተመለሰ። የሳኦልም ልጅ ሜልኮል ዳዊትን ለመቀበል ወጣችና። ምናምንቴዎች እርቃናቸውን እንደሚገልጡ የእስራኤል ንጉሥ በባሪያዎቹ ቁነጃጅት ፊት እርቃኑን በመግለጡ ምንኛ የተከበረ ነው! አለችው። ዳዊትም ሜልኮልን፦ በእግዚአብሔር ፊት ዘፍኛለሁ በእግዚአብሔር ሕዝብ በእስራኤል ላይ አለቃ እሆን ዘንድ ከአባትሽና ከቤቱ ሁሉ ይልቅ የመረጠኝ እግዚአብሔር የተባረከ ይሁን ስለዚህም በእግዚአብሔር ፊት እጫወታለሁ። አሁንም ከሆንሁት ይልቅ የተናቅሁ እሆናለሁ፥ በዓይንሽም እዋረዳለሁ ነገር ግን በተናገርሽው ቁነጃጅት ዘንድ እከብራለሁ አላት።
>
> 2ኛ ሳሙኤል 6፡20-22

5. ታላቅ ቤተክርስቲያንን የሚገነባ መጋቢ ወንጌል ስርጭትን ለመሥራት ጠንካራ ውሳኔዎችን መስጠት የሚችል መሆን አለበት።

ቤተክርስቲያንን እንደ ሰራዊት ለመምራት ብርታት ይጠይቃል። የአሁድ ክርስቲያንን ወደ ወንጌል ማዳረስ ድባብ ውስጥ ለመክተት ጉልበት ይሻል። ገንዘብን ወዳጅ ለሆነና ብልጽግና ናፋቂ ለሆነ ማኅበር የወንጌልን አስፈላጊነት ለመስበክ አቅም ይፈልጋል።

> ወሬውም በኢየሩሳሌም ባለችው ቤተ ክርስቲያን ስለ እነርሱ ተሰማ፥ በርናባስንም ወደ አንጾኪያ ላኩት፤ እርሱም መጥቶ የእግዚአብሔርን ጸጋ ባየ ጊዜ ደስ አለው፥ ሁሉንም በልባቸው ፈቃድ በጌታ ጸንተው ይኖሩ ዘንድ መከራቸው፤ ደግ ሰውና መንፈስ ቅዱስ እምነትም የሞላበት ነበረና። ብዙ ሕዝብም ወደ ጌታ ተጨመሩ።
>
> የሐዋርያት ሥራ. ፲፩:22-24

6. ታላቅ ቤተክርስቲያንን የሚገነባ እረኛ አጥቢያዎችን ይከፍቱ ዘንድ ሰዎችን ለመላክ ጠንካራ ውሳኔ ማሳለፍ መቻል አለበት።

ሰዎችን መላክ ቀላል ነገር አይደለም። ከምንወዳቸው ሰዎች ጋር መቆየት ያስደስተናል። ሆኖም ይህ የቤተክርስቲያንን እድገት የሚገድል ነገር ነው።

> በዚያን ጊዜም ከጦሙ ከጸለየም እጃቸውንም ከጫኑ በኋላ አሰናበቱአቸው።
>
> የሐዋርያት ሥራ ፲፫:3

7. ታላቅ ቤተክርስቲያንን የሚገነባ መጋቢ ሰዎችን በተለያየ መንገድ ለማስተናገድ ጠንካራ ውሳኔ ማሳለፍ መቻል አለበት።

ሰዎችን እግዚአብሔር በሰጣቸው ስጦታ መሠረት ማስተናገድ ቀላል አይደለም። ብዙውን ጊዜ ሰዎች ራሳቸውን ከሌሎች ጋር ያወዳድራሉ። እንዲህ ሲሉም ይጠይቃሉ፤ "ይህ ሰው የሚያደርገው ነገር ምንድን ነው? እኔስ ምን እያደረግሁ ነው? ይህ ሰው እያገኘ ያለው ምንድን ነው? እኔስ ምን እያገኘሁ ነው? ይህ ሰው ወዴት እየሄደ ነው? እኔስ የማልሄደው ለምንድን ነው?"

ምክንያቱም መሪዎች ሰዎችን በተለያየ መንገድ ማስተናገድ ያስፈራቸዋል፤ስለሆነም ትክክለኛ ያልሆኑ ሰዎችን በተሳሳተ ቦታ አስቀምጠው ትክክለኛ ያልሆነን ነገር እንዲያደርጉ ይተዋቸዋል።

> ጴጥሮስም ይህን አይቶ ኢየሱስን። ጌታ ሆይ፥ ይህስ እንዴት ይሆናል? አለው። ኢየሱስም፦ እስክመጣ ድረስ ይኖር ዘንድ ብወድስ፥ ምን አግዶህ? አንተ ተከተለኝ አለው።
>
> ዮሐንስ. 21፡21-22

8. ታላቅ ቤተክርስቲያንን የሚገነባ መጋቢ ግንባታን ያደርግ ዘንድ ጠንካራ ውሳኔ መስጠት መቻል አለበት።

ግንባታ ብዙ ነገሮችን የሚያካትት ነው። ነህምያ ብዙ ዋጋ የከፈለበት ምክንያት የኢየሩሳሌምን ቅጥር ለመሥራት በመወሰኑ ነው። ብዙውን ጊዜ የእግዚአብሔርን ቤት መሥራት መንፈሳዊ ውጊያ መዋጋትን፣ በዚያውም ልክ ግንባታን ያካትታል።

> ቅጥሩንም የሚሠሩትና ተሸካሚዎቹ በአንድ እጃቸው ይሠሩ ነበር፥ በአንድ እጃቸውም የጦር መሣሪያቸውን ይይዙ ነበር። አናጢዎቹም ሁሉ እያንዳንዱ ሰይፉን በወገቡ ታጥቆ ይሠራ ነበር ቀንደ መለከትም የሚነፋ በአጠገቤ ነበረ።
>
> ነህምያ. 4፡17-18

9. ታላቅ ቤተክርስቲያንን የሚገነባ መጋቢ ሰዎች ገንዘባቸውንና ያላቸውን ሁሉ እንዲሠዉ ጠንካራ ውሳኔ ማድረግ ይኖርበታል።

ሰዎች ኑሮዋቸውን መሥዋዕት እንዲያደርጉ ማድረግ ቀላል አይደለም። ወደተረጋገጠው ሞታቸው ለመላክ ጠንካራ አዛዥ ያስፈልጋል።

> ኢየሱስም ይህን ሰምቶ። አንዲት ገና ቀርታሃለች፤ ያለህን ሁሉ ሸጠህ ለድሆች ስጥ፥ በሰማይም መዝሙርጎ ታኖራለህ፥ መጥተህም ተከተለኝ አለው።
>
> ሉቃስ 18፡22

10. ታላቅ ቤተክርስቲያንን የሚገነባ መጋቢ በጸሎት ሰዓታት ሕዝቡን ለመምራት ውሳኔ ማሳለፍ ይኖርበታል።

ለሰዓታት ጸሎት ሰዎችን በጸሎት መምራት ቀላል አይደለም።

ማኅበሩን አስገድዶ የረጅም ሰዓታት ጸሎት እንዲያደርጉ ለማስቻል ጠንካራ መሪ ያስፈልጋል።

ወደ ደቀ መዛሙርቱም መጣ፤ ተኝተውም አገኛቸውና ጴጥሮስን። እንዲሁም ከእኔ ጋር አንዲት ሰዓት እንኳ ልትተጉ አልቻላችሁምን?

ማቴዎስ 26፡40

11. ታላቅ ቤተክርስቲያንን የሚገነባ መጋቢ በቤተክርስቲያን ቆጣቢነትን መለማመድ ይኖርበታል። ቆጣቢ መሆንና በቆጣቢነት የሕይወት ዘይቤ ሰዎችን መምራት ቀላል አይደለም። ጠንካራና ብርቱ መሪ መሆን ካልቻልህ ተቋምህን ወደ ቆጣቢነት መርህ ማስገባት አትችልም።

ከጠገቡም በኋላ ደቀ መዛሙርቱን። አንድ ሰንኳ እንዳይጠፋ የተረፈውን ቍርስራሽ አከማቹ አላቸው።

ዮሐንስ. 6፡12

12. ታላቅ ቤተክርስቲያን የሚገነባ መጋቢ በአስቸጋሪና በከባድ ጊዜያት ሁሉ ማኅበሩን በሙሉ ወደ ጸም መውሰድ የሚችል መሆን አለበት።

አዋጅም አስነገረ፥ በነነዌም ውስጥ የንጉሡንና የመኳንንቱን ትእዛዝ አሳወጀ፥እንዲህም አለ፦ ሰዎችና እንስሶች ላሞችና በጎች አንዳችን አይቅመሱ አይሰማሩም ውኃንም አይጠጡ

ሰዎችና እንስሶችም በማቅ ይከደኑ፥ ወደ እግዚአብሔርም በብርቱ ይጩኹ ሰዎችም ሁሉ ከክፉ መንገዳቸውና በእጃቸው ካለው ግፍ ይመለሱ።

ዮናስ. 3፡7-8

13. ታላቅ ቤተክርስቲያንን መገንባት የሚፈልግ መሪ አንዳንድ ሰዎችን ለማስወገድና በሌሎች ለመተካት የጨከነ መሆን ይኖርበታል።

ንጉሡም ከሴቶች ሁሉ ይልቅ አስቴርን ወደደ፥ በዓይኑም ከደናግል ሁሉ ይልቅ ሞገስንና መወደድን አገኘች የመንግሥቱንም ዘውድ በራስዋ ላይ አደረገ፥ በአስጢንም ፋንታ አነገሣት።

አስቴር. 2፡17

14. ታላቅ ቤተክርስቲያንን መገንባት የሚፈልግ መጋቢ በሕዝቡ ፊት ተገቢውን ክብር ለማግኘት ጠንካራ ውሳኔ ያስፈልገዋል።

ብዙውን ጊዜ መጋቢ ስለ ራሱ ማለት ያለበትን የሚናገርለት የለም። ስለዚህ ለማጎበሩ ራሱ መናገር ይኖርበታል። አንዳንድ ጠንካራ ነገሮችን የሚናገርልህ ከሌለ ራስህ መናገር ልመድ።

መጋቢያቸው እንደሆንሁ ለቤተክርስቲያኔ መናገር ነበረብኝ። እኔንም እንዴት መናገር እንዳለባቸው አስታውቃቸዋለሁ። በሌላ ጊዜ ደግሞ ቢሾፓቸው መሆኔን መንገር ችዬአለሁ።

> ኤልያስም አላት። አትፍሪ ይልቅስ ሄደሽ እንዳልሺው አድርጊ አስቀድመሽ ግን ከዱቄቱ ለእኔ ታናሽ እንጎቻ አድርገሽ አምጭልኝ፥ ከዚያም በኋላ ለአንቺና ለልጅሽ አድርጊ።
>
> 1ኛ ነገሥት. 17፡13

ክፍል 13

የቤተክርስቲያን እድገትና ከሌላው የመቅዳት ዘዬ

ምዕራፍ 32

ከሌላው የመቅዳት ጥበብ

ቅጂ ማለት ምሳሌንና ሥርዓትን የመከተል ጥበብ ሲሆን ይህም ዋናውን ለመምሰል የሚደረግ ጥሩ ኩረጃ ነው።

ሁሉም ስኬትን የተጎናጸፉ መጋቢያን ከሌላው ቀድተዋል። የቤተክርስቲያን እድገት እውን ሊሆን የሚችለው ከሌላው ለመቅዳት ፈቃደኞች በሆኑ መጋቢያን አማካይነት ነው። የምትፈልገውን ነገር ከተለማመደ ሰው መቅዳት ነውር የለውም።

መቅዳት የሚለው ቃል ምናልባት ለአንተ ጥሩ ቃል ላይሆን ይችላል። ነገር ግን መቅዳት ስሕተት የሚሆነው በፈተና ጊዜ በሕገ ወጥ መንገድ ሲከወን ነው። መቅዳት ታላቅ የመማሪያ ደረጃ ሲሆን ልጆችና ሕፃናት የሚማሩበት ከእግዚአብሔር የተሰጠ መንገድ ነው።

"ከሌሎች የማትኮርጅ ሁን" የሚሉ ሰዎች አሉ፤ እውነታው ግን እንደዚያ አይደለም። እያንዳንዱ ከሌላው ቀድቷል። እያንዳንዱ ታላቅ የአምልኮ መሪ ከሌላ የአምልኮ መሪ ቀድቷል። እያንዳንዱ ታላቅ ወንጌላዊ ከሌላ ወንጌላዊ ቀድቷል። እያንዳንዱ ታላቅ የእግዚአብሔር ሰው ከሌላው ታላቅ የእግዚአብሔር ሰው ቀድቷል።

እያንዳንዱ ቅባት የሌላው ቅባት ቅጂ ነው። በጴጥሮስ፣ በያዕቆብና ዮሐንስ ላይ የመጣው ቅባት ከጌታቸው ከኢየሱስ የተቀዳ ነው።

በኤልሳዕ ላይ የነበረው ቅባት ከኤልያስ ላይ የተቀዳ ነው።

በቅርብ ጊዜ በአንድ የአፍሪካ አገር ውስጥ ሆቴል ቁርስ እየበላሁ ሲዲውና ሙዚቃው በዓለም ዙሪያ ከሚደመጥለት ክርስቲያን ዘማሪ ጋር ተገናኘሁ። አብረን ተቀምጠን ሳለን ከመጋቢዎቼ አንዱ እንዲህ ሲል ዘማሪውን ጠየቀው፤ "ለመሆኑ በዚህ በዝማሬ አገልግሎት በጎ ተጽዕኖን ያሳረፈብህ ማን ነው?"

“አንድሬ ክራውች ለእኔ ታላቅ መነሣሣት የሆነ ሰው ነው” በማለት መለሰ።

ወዲያውኑ ይህ ሰው እንደዚህ ባለ መልካም ሁኔታ ሊሳካለት እንደቻለ ተገነዘብሁ። ምክንያቱም በቀላሉ ሌላውን መቅዳት ስለቻለ ነው። ሌላውን ሰው መምሰል በመቻሉም ኩራት ተሰምቶታል።

በማንኛውም መስክ ጥሩ መሥራት የቻሉ ሰዎች በሚገባ ሌሎችን በመምሰል የተከተሉ ሰዎች ናቸው። የስብከት ቢሆን፣ የዝማሬ፣ የፈውስ፣ የእረኝነት አገልግሎት መርሁ አንድ ነው። እግዚአብሔር ብዙ ተመሳሳይ የሆኑ አገልጋዮች ማፍራት ይፈልጋል።

እንዴት መቅዳት እንደሚገባህ

የትልቅና የምታድግ ቤተክርስቲያን መጋቢ ለመሆን ወስን። ቤተክርስቲያንህ እድገት እንዲኖራት ማድረግ ይቻልሃል። ታላቅ የእግዚአብሔር ሰው ለመሆን ቁርጥ ውሳኔ አድርግ። የግዙፍ ቤተክርስቲያን መጋቢ ለመሆን ወስን። ይህን እንዴት ማድረግ ትችላለህ?

መልሱ ቀላል ነው፤ ካንተ ቀድሞ የተሠራውን ቅዳ። በእግዚአብሔር ታላቅነት ውስጥ ለመግባት ልዩ ምትሃታዊ ቀመር መሥራት አያስፈልግህም። የግድ ቁጥቋጦ ሲቃጠል ማየት የለብህም። በቀጥታ በእግዚአብሔር ታላቅ ወደ ምትሆንበት መንገድ ግባ።

በሕያውነት እየተንቀሳቀሱ ያሉ ቤተክርስቲያናት እየተመሩ ያሉት በተመሳሳይ መጋቢያን ነው። እያደጉ ያሉ ቤተክርስቲያናት እየተመገቡ ያሉት ተመሳሳይ በሆኑ ወንዶችና ሴቶች ነው። እንግዲህ ‘ያ ራእይህ ከሆነ ለምን ታዲያ አንተም እነዚህን ሰዎች አትመስልም?

መቅዳት የመቀባት መንገድ ነው። በእግዚአብሔር ከፍ የምትልበት ቁልፍ ነው።

መቅዳት ከእግዚአብሔር መንግሥት ጋር ወደተያያዙ ነገሮች የምትገባበት በር ነው።

ታላቅ ወንጌላዊ ካለ እርሱን የሚመስል ሌላ ታላቅ ወንጌላዊ ይነሣል። የተቀባ መጋቢ ካለ ልክ እርሱን መሰል ሌላ መጋቢ ይቀባል። ብርቱ ሐዋርያ ካለ እርሱን የመሰለ ሌላ ብርቱ ሐዋርያ ይወጣል።

አንተ የተለየህ ወይም በዓይነትህ ብቸኛው አይደለህም። አግዚአብሔር አስቀድሞ ያስነሣውን ሌላኛውን የምትመስል ነህ። ተመሳሳይ ጥሪ ያለውን ሰው ፈልግና አጥብቀህ ተከተለው።

ወደ ቤታችን መሄጃችን ጊዜው ቅርብ ነው፤ ሩቅ አይደለም። ስለዚህም ለስሕተቶችና ለሕጸጾች በቂ ጊዜ የለህም። ለሙከራ ጊዜ ማባከን አይኖርብህም። ምናልባት ጌታ በሚጠራህ ወቅት በሙከራህ መሐል ልትሆን ትችላለህና።

ወደ ዋናው ነጥብ በቀጥታ መምጣት ይኖርብሃል። ቅባቱ በአፋጣኝ ያስፈልግሃል። በሚገባ መስበክ አለብህ፤ ጊዜውም አሁን ነው! በዚህ ጌታ በሰጠህ ጊዜም በሽተኛን ልትፈውስ፤ የሞተን ልታስነሣ ያስፈልጋል።

ራስህን ትሁት አድረገህ ከሌላው ስኬት እንደ መቅዳት በማይረባ ሥራ ራስህን ለዓመታት በሙከራ ውስጥ ማሰማራት አይኖርብህም።

ሁላችንም የሌሎች ቅጂዎች ነን

በመጀመሪያ ሁላችንም የሌሎች ቅጂዎች እንደሆንን እመን። ለመጨረሻው ዘመን ክርስቶስ የመረጠንና የጠበቀን ብርቅዬዎች ነን ብዬ አላስብም። እንደዚህ ዓይነት እሳቤ ወደ ስሕተት ይመራል። የጌታ ሰራዊት አባል ነኝ። በሥልጣን ደረጃዬ የምገኝ ስሆን አባቶቼ ከሠሩት ውስጥ እኔም መቅዳት በመቻሌ ደስ ይለኛል።

ታላቅ ቤተክርስቲያንን ማስነሣት ትፈልጋለህ?

የቤተክርስቲያንን እድገት ትሻለህ?

ለየት የማለት ሐሳብ ካለህ ግን ፊትህ ከተቀመጡት ምሳሌዎች የመማርን እድል እንድታጣ ያደርግሃል። እግዚአብሔር በዛ ያሉ የግዙፍ ቤተክርስቲያናት መጋቢያን ማስነሣት ይፈልጋል።

መቅዳት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነውን?

ምድርም ዘርን የሚሰጥ ሣርንና ቡቃያን እንደ ወገኑ ዘሩም ያለበትን ፍሬን የሚያፈራ ዛፍን እንደ ወገኑ አበቀለች። እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደ ሆነ አየ። . . . እግዚአብሔርም ታላላቆች አንበሪዎችን፥ ውኃይቱ እንደ ወገኑ ያስገኙቻቸውንም ተንቀሳቃሾቹን ሕያዋን ፍጥረታት ሁሉ፥ እንደ ወገኑ የሚበሩትንም ወፎች ሁሉ ፈጠረ እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደ ሆነ አየ። . . እግዚአብሔር የምድር አራዊትን እንደ

ወገኑ አደረገ፥ እንስሳውንም እንደ ወገኑ የመሬት ተንቀሳቃሾችንም እንደ ወገኑ አደረገ እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደ ሆነ አየ።

ዘፍጥረት. 1፡ 12፤21፤25

ሁሉን ቻይ የሆነው እግዚአብሔር ፍጥረት ራሱን የሚመስለውን እንዲያፈራ አደረገ። ሳር እርሱን የሚመስል ወገኑን፣ ቡቃያም እንዲሁ፣ ዓሣ ነባሪዎችም ራሳቸውን የሚመስሉ እንዲያፈሩ አደረገ። ሰውም ራሱን የሚመስልን ሌላ ሰው አፈራ። ጌታ እግዚአብሔር ይህ ተመሳሳይ ወገን የማፍራት ነገር መልካም እንደሆነ አይቷል! የተለየን ነገር ከማፍራት ይልቅ ጥሩ ቅጂ በማድረግ ፍሬን እናፍራ።

እግዚአብሔርም አለ፦ ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር. . .

ዘፍጥረት 1፡26

እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር፣ እርሱን የሚመስል አድርጎ ነው። እኛን የሚመስል እንፍጠር አለ፣ ተመሳሳይ ሌላ ቅጂ። በእግዚአብሔር አምሳል በመፈጠራችን ምክንያት በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ብዙ መመሳሰል አለ። እግዚአብሔር መንፈስ ሲሆን የመናፍስት አባት ነው።

የሰው ልጆች በሥጋ ውስጥ የሚኖሩ መናፍስት ናቸው። እንደምናውቀው እግዚአብሔር አብ፣ እግዚአብሔር ወልድና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ሥላሴን ያሳዩናል።

ሰውም የመንፈስ፣ ነፍስና ሥጋ የሦስትዮሽ ውህድ ነው። ሰዎች በፈጠራና ግኝቶች ሲንቀሳቀሱ በግልጽ የሚያሳየን ከእግዚአብሔር እንደቀዱ ነው።

ምዕራፍ 33

መቅዳት እንዴት ለአገልግሎትህ ሊጠቅምህ እንደሚችል

ቅጂ ከፍተኛው እና ፈጣኑ የመማሪያ ዓይነት ነው።

1. ቅጂ ለልጆች ከእግዚአብሔር የተሰጠ የመማሪያ መንገድ ነው።

ልጆች ያለ ምንም ጥረት ይህንን ስጦታ ስለሚጠቀሙበት በቀላሉ መማር ይችላሉ። በዚህም ምክንያት ልጆች በቀላሉ ቋንቋን ይማራሉ። ብዙ አዳዲስ ነገሮችን ለማስመሰል ቢፈተኑም ታዳጊዎች አዳዲስ ነገሮችን የመማር ችግር የለባቸውም፣ ምክንያቱም ከመቅዳት የሚያግዳቸው ምንም ስለሌለ ነው።

አንድ ቀን አንድ ሰው ስለ ሰዎች ሲያወራ "ቢቢቲ" ናቸው ሲል ሰማሁ። ይህም "ቦርን ቢፎር ቴክኖሎጂ" (ከቴክኖሎጂ ቀድመው የተወለዱ) ማለት ነው። ቀጠለና "እኔም ከቴክኖሎጂ ቀድሜ የተወለድሁ ነኝ። እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች ኮምፒውተሮችንና ሌሎች ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን ለመማር ይቸገራሉ።" አለ። በመጨረሻም "የቢቢቲ ችግር ያለባቸው ሰዎች ኃላፊነት ሲሰጣቸው ቤተክርስቲያን ወደፊት ለመገስገስ ተግዳሮት ይገጥማታል።" ሲል አከለ።

እኔም እንዲህ ስል ማሰብ ጀመርሁ "አንድን ሰው ቢቢቲ (ከቴክኖሎጂ በፊት የተወለደ) የሚያስብለው ፈጣን በሆነው በመቅዳት ጥበብ ያለመማር ችግሩ ነው! በቀላሉ ስለማይቀዳ ኮምፒውተሮችን፣ ሶፍት ዌሮችንና ሌሎች ዘመናዊ መሣሪያዎችን መረዳት ያቅተዋል!"

2. መቅዳት ራስህን ትሁት የምታደርግበት የእግዚአብሔር መንገድ ነው።

. . ያለ እኛ ፍጹማን እንዳይሆኑ

ዕብራውያን 11፡40

በዓለም የተለመደው ጥሩ የመማሪያ መንገድ ት/ቤት መሄድ ነው። በአገልግሎት ውስጥ የመማሪያው መጽሐፍ ቅዱሳዊው መንገድ ግን መቅዳትና መከተል ናቸው። መቅዳት እግዚአብሔር አገልጋዮችን የሚያበዛበት ተፈጥሮአዊው መንገድ ነው። ትዕቢትና አጉል እምነት ታላላቅ የተቀቡ አገልጋዮች እንዳንሆን ያደርገናል።

እንደ አንዳንድ ሰዎች ሥራዎችህን ማከናወን ችለህ ቢሆን ኖሮ ምን ያህል ትልቅ ስኬት ላይ ትደርስ እንደነበር አስበው። ከሌሎች መብለጥን እርሳው! ነገር ግን ካንተ ቀደም ያሉትን ሰዎች እንኳ ብትመስል ብዙ ስኬት በተጎናጸፍህ ነበር።

አገልግሎት አስቸጋሪ ነገር ነው። እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት እንኳ ብዙ ጸጋ ያስፈልጋል።

> እኔም አብን እለምናለሁ ለዘላለምም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል፤
> ዮሐንስ. 14፣16

መንፈስ ቅዱስ (አጽናኙ) ቅባት ነው። ኢየሱስ እንደ እርሱ ያለ ሌላ አጽናኝ እንደሚመጣ ሲናገር ሌላ ተመሳሳይ ቅባት እንደሚመጣ ቃል እየገባ ነበር። በሚሄድበት ጊዜ እርሱ ሲያገለግልበት የነበረው ተመሳሳይ ቅባት ለሐዋርያትም እንደሚሰጣቸው አስታወቃቸው።

ብዙ መጋቢያን ይህንን ቀላል እውነት መረዳት ቢችሉ በአገልግሎታቸው እድገትን ማፋጠን በቻሉ ነበር። እግዚአብሔር ሊሰጥህ የሚፈልገው ልዩና አዲስ ቅባት የለም።

የሚሰጥህ ከዚህ በፊት የተሰጠን ተመሳሳይ ቅባት ነው።ሐዋርያት እንኳ የተቀበሉት ተመሳሳይ ቅባት ነው።

ኦርጅናል (በዓይነትህ የመጀመሪያው) እንዳልሆንህ መቀበል ትህትና ይጠይቃል። ሰዎች በአገልግሎትህ ተመስጠው ከሆነ መልእክትህ ኦርጅናል እንዳልሆነ ለማወቅ ቀላል አይሆንም። በአቀራረብህም ተስበው ከሆነ ከሌላ ቦታ የተማርከው እንደሆነ ለመግለጥ አስቸጋሪ ነው።

ከሌላው መቅዳት እንደ በግ ጥገኛ ያደርግሃል። የበግ ባሕርይ ከእባብ ባሕርይ ፈጽሞ ይለያል። እባቦች ብቸኝነትና ጥገኛ አለመሆን ይታይባቸዋል። ከጌታ ጋር ለመራመድ ከፈለግህ ከዚህ ፍጹም ተቃራኒ መሆን ይጠበቅብሃል።

የሌላ አምሳያ መሆን ከፈለግህ ልትደገፍበት የሚገባ ሰው ይኖራል። ልትማርበት የሚገባህና ልትከተለው የሚያስፈልግህ ሰው ይኖራል። ይህ ደግሞ መልካም ነገር ነው፤ ምክንያቱም ማንም ሁሉን በፈጠረ በጌታ እንጂ በምንም መመካት አይችልም።

ትሁት በመሆንህም ምክንያት የእግዚአብሔር በረከቶች በሌላም ትውልድ ይቀጥላሉ።

ለዚህ ትውልድ አንድ ታላቅ የእግዚአብሔር ሰው መነሣቱ ሳይበቃ ለሚቀጥለውም ትውልድ ተመሳሳይ ነገር ይሆናል።

3. መቅዳት ከጸሐይ በታች ምንም አዲስ ነገር እንደሌለ ያስገነዝብሃል።

> የሆነው ነገር እርሱ የሚሆን ነውቱ የተደረገውም ነገር እርሱ የሚደረግ ነው ከፀሐይም በታች አዲስ ነገር የለም።
>
> ማንም። እነሆቱ ይህ ነገር አዲስ ነው ይል ዘንድ ይችላልን? እርሱ ከእኛ በፊት በነበሩት ዘመናት ተደርጎአል።
>
> መክብብ 1፡9-10

በእርግጥ ከጸሐይ በታች አዲስ ነገር የለም። ይህን እውነታ ልትቀበለው የተገባ ነው። ልታቀርበው የምትችለው ምንም ዓይነት አዲስ ነገር የለም። እንዲሁም በሕይወትህ ምንም ለየት ያለ ነገር ማስተዋወቅ አትችልም።

እንደ ሌሎች አገልጋዮች እኔም አንድ ወቅት አዲስን ነገር ለማሳየት ፈለግሁ። ማንም ያላገኛቸው አዳዲስ ስጦታዎችና ሐሳቦች እንዳሉኝ አሰብሁ።

ከጊዜ በኋላ ግን እኔ ያሰብሁት ሁሉ ከዚህ በፊት የተሠራ መሆኑን አስተዋልሁ። እያንዳንዱ ያደረግሁትና የተናገርሁት ሁሉ ከእኔ በፊት የነበሩ ሰዎች እንደተናገሩት እንዲሁም እንዳደረጉት ተረዳሁ።

ስለ አገልግሎቴ የሆነው ተጨባጩ ነገር በእውነተኝነት የማደንቃቸውን ሰዎች በታይል መከተሌ ነው። እነርሱን መሆን እፈልግ ነበር። ይህንንም በመናገሬ አላፍርም። መንፈሳቸውን እወደዋለሁ! አደራረጋቸውንም አደንቃለሁ! በትክክል ሊሠራ የሚችልን ነገር ብቀዳ ለእኔ ያ ትልቅ ክንዋኔ ነው።

4. መቅዳት በጎ የሚሆንበት ምክንያት ፍሬ ያላቸውና ስኬታማ የሆኑ ሰዎችን እንድትመስል ስለሚያደርግ ነው።

መቅዳት ከመከራ ነፃ ያወጣሃል። አንድ ሁልጊዜም ሊሠራ የሚችል መርህ በመፈለግ እድሜህን ከማባከን ያድንሃል።

አዲስ ስም መፍጠር አያስፈልግህም። ስም መሰየም ቀላል አይደለም። ስሞች በንግድ ዓለም ውስጥ የሚሸጡት ለዚህ ነው። መልካም ስም በምድር ላይ ዋጋ ካላቸው ነገሮች አንዱ ነው። የሌላው ተመሳሳይ መሆን ማለት ሌላ ዓይነት ተመሳሳይ ስም መያዝ ነው። መቅዳት ለቀደሙት መሰሎችህ ያገለገሉትን ስልቶችና ቀመሮችን እንድትጠቀም ይረዳሃል።

እንደ ሌላው ዓይነት መሆን ስፈልግ ማወቅ የምፈልገው ነገር ቢኖር የምቀዳው ሰው የሚጠቀማቸውን መንገዶች ነው። ለእርሱ የሠራ ስልት ለእኔም ይሠራል። የሚጠበቅብኝ ለእርሱ ውጤት ያመጡለትን ስልቶችና ቴክኒኮችን መቅዳት ብቻ ነው። ተመሳሳይ ዓይነት ነገር ስለምፈልግ ከዚህ ቀደም የሠሩት መንገዶች ለእኔም በእርግጠኝነት ይሠሩልኛል!

5. መቅዳት በዚህ የአገልግሎት ጎዳና ላይ ነገሮችን ያቀልልሃል።

ወደ አገልግሎት የተጠሩ ብዙ ሰዎች በአገልግሎት ጎዳና ላይ እንዴት መራመድ እንዳለባቸው አያውቁም። እግዚአብሔር እንደጠራቸው ያውቃሉ፤ ሆኖም ግን እንዴት ማደግ እንዳለባቸው አያውቁም።

ብዙ የእግዚአብሔር ሰዎች ከፍ ወዳለ የአገልግሎት ከፍታ እንዴት መውጣት እንዳለባቸው አይረዱም። ሌሎች የእግዚአብሔር ሰዎች ታላላቅ ነገሮችን ሲከውኑ ያያሉ፤ እነርሱ ራሳቸው ግን ያንን እንደሚያደርጉ አያምኑም!

አሁን አንድ ዓይነት ተመሳሳይ ነገሮችን የመከወኛው መንገድ ግልጽ ሆኗል። ራስህ ዝቅ አድርግና ሌላ ተመሳሳይ ዓይነት ሰው ሁን።

ልዩ፣ ምርጥና የተለየ ለመሆን አትጣጣር። ሊሠራ የሚችል የሌላ ሰው ቅጂ ሁን። ሌሎች የተጠቀሙትን ቴክኒኮች ውሰድ። በቅርበት ተከተላቸው። እነርሱ የሰበኩትን ስበክ። እንዲሁም እነርሱ

እንደጸለዩት ጸልይ። እግዚአብሔርን በሚፈልጉበት መንገድ አንተም ፈልገው። እነርሱ በሚያደርጉበት መንገድ ከእግዚአብሔር ጋር ጎብረት አድርግ። ስኬታማ የሆነ አስገራሚ ቅጂ ሆነህ ራስህን ታገኘዋለህ።

6. መቅዳት ወደ አዲስ ነገር ፈጥነህ እንደትገባ ያደርግሃል።

ቅጂ በሕይወትና በአገልግሎት ውስጥ የሚኖርህን ግስጋሴ ያፋጥነዋል። በሚገባ የተጠና መንገድ በመሄድህ ከዚህ በፊት ሄደውበት ያተረፉት ሰዎችን ዓይነት ጥቅም ታገኛለህ። እነርሱን ያዘገያቸው አንተን አያዘገይህም። እንቅፋቶችን ሁሉ በፍጥነት ጥሰህ ታልፋለህ፤ ምክንያቱም የቀደመ አምሳያህ እንዴት ማሸነፍ እንዳለብህ መንገድ ስለቀደደልህ ነው።

ያለ አንዳች ሙከራና ፈተና ከሆነ ማንኛውም ሰው በፍጥነት መጓዝ ይችላል። አንድ ቀን ከሆነ ሰው ጋር ወደ አንድ ስፍራ እሄድ ነበር። እርሱ ከፊት እኔ ከኋላ ሆነን በተለያየ መኪና ውስጥ ነበርን። መንገዱ ተዘጋግቶ ስንቸገር ጊዜ ደወለልኝና በዚያ መንገድ የመኪና መጨናነቅ ስላለ እንዳልሄድ አሳሰበኝ። በመጨረሻ ካሰብሁበት ስፍራ በፍጥነት ደረስሁ፤ ምክንያቱም እርሱ ባለፈበት ችግር ውስጥ እንዳላልፍ አድኖኛልና ነው።

7. መቅዳት ችግሮችን በአሸናፊነት እንደትወጣ ይረዳሃል።

የተወሰኑ ችግሮች መፍትሄያቸውም አንድ ዓይነት ነው። ከአንድ ሰው ስትቀዳ መፍትሄያቸውንም ካካበቱት ልምድ ልታገኝ ትችላለህ። ተመሳሳይ ችግሮችን ለማስወገድ የተጠቀሙባቸው መፍትሄዎቻቸውም ያንተ ይሆናሉ።

በድንገተኛ አደጋ ጊዜ ዶክተሮች ለምን እንደሚረጋጉ ይገርምሀል? ምክንያቱ ተመሳሳይ የሆኑ ችግሮች በየጊዜው ስለሚገጥማቸውና መፍትሄዎችም ስላስቀመጡ ነው።

8. መቅዳት ተፈጥሮአዊው የመባዣ መንገድ ነው።

አምሳያን መተካትና መራባት የፍጥረት ተፈጥሮአዊው መንገድ ነው።

> ምድርም ዘርን የሚሰጥ ሣርንና ቡቃያን እንደ ወገኑ ዘሩም ያለበትን ፍሬን የሚያፈራ ዛፍን እንደ ወገኑ አበቀለች።እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደ ሆነ አየ።እግዚአብሔርም ታላላቆች አንበሪዎችን፥ ውኃይቱ እንደ ወገኑ ያስገኘቻቸውንም ተንቀሳቃሾቹን ሕያዋን ፍጥረታት ሁሉ፥ እንደ ወገኑ. . . ፈጠረ።እግዚአብሔር የምድር አራዊትን እንደ ወገኑ አደረገ፥ እንስሳውንም እንደ ወገኑ፥ የመሬት ተንቀሳቃሾችንም እንደ ወገኑ አደረገ እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደ ሆነ አየ።
>
> ዘፍጥረት 1፡12፣21፣25

ቤተክርስቲያን ከክብር ወደ ክብር የምትሸጋገርበትና የምታድግበት መንገድ ያለ ሐፍረት ከቀደሙት በመማር ነው። ሌሎች ወደ ፊት የሚያስጓጓት መንገዶች እንዳሉ አይካድም። ሆኖም ግን ለእኔ የሠራልኝን ነገር ማካፈል እችላለሁ። መቅዳት! መቅዳት! መቅዳት! ሌላውን መሆን። ከእኔ በፊት ቀድመው የሄዱትን አባቶች መምሰል እፈልጋለሁ። ኢየሱስን መምሰል እሻለሁ። ለየት ያለ ማንነት እንዲኖረኝ አልፈልግም።

9. መቅዳት የታላቅ ትምህርትና ስብከት ቁልፍ ነው።

> ሌላ ምሳሌ ስሙ። የወይን አትክልት የተከለ ባለቤት ሰው ነበረ፤ ቅጥርም ቀጠረለት፥ መጥመቂያም ማሰለት፥ ግንብም ሠራና ለገበሬዎች አከራይቶ ወደ ሌላ አገር ሄደ።
>
> ማቴዎስ 21፡33

ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ቃል እጅግ በተዋበና በተቀባ መንገድ አስተምሯል። ትናንሽ ልጆች መጽሐፍ ማንበብ ካቆሙ በኋላ እንኳ ረጅም ጊዜ በኋላም ቀድሞ ያነበቡትን ያስታውሱታል። የክርስቶስ ትምህርቶች ከሁለት ሺህ ዓመታት በኋላ እንኳ በጣም አስፈላጊዎች ናቸው።

ኢየሱስ የተናገራቸው ነገሮች በብዙ ሰዎች ተነበዋል፤ በብዙ ጸሐፍት ተጠቅሰዋል፣ ወደ ብዙ ቋንቋዎችም ተተርጉመዋል፤ በብዙ ዓይነት መንገድ ተዘምረዋል፣ በብዙ ሥነ ጥበባት ተገልጸዋል።

አንድ ሰው፣ ‹ሶቅራጥስን፣ ፕላቶን እና አሪስቶትልን ከኢየሱስ ጋር ማስተያየት ያልተመለሰን ጥያቄ ከመገለጥ ጋር እንደማስተያየት ነው› ብሏል።

ከዓመታት በፊት ለፍቅረኛዬ ልክ እንደ ኢየሱስ ዓይነት የቃሉ አስተማሪ መሆን እንደምፈልግ ነግሬኟት። ለራሴ እንዲህ ስል አሰብሁ፣ “የኢየሱስ ትምህርቶች በሕፃናት እንኳ በቀላሉ የማይረሱ

ነበሩ።" ኢየሱስን ልኮርጅ ወሰንሁ። መጋቢ ከመሆኔ ከዓመታት በፊት ቃሉን በታሪኮች እያዋዛሁ ለማስተማርና ለመስበክ ወሰንሁ።

ኢየሱስ ብዙ ታሪኮችን ነግሮናል። "አንድ ሰው ሁለት ልጆች ነበሩት". . .አንድ ሰው ታላቅ ግብጥ አዘጋጀ. . .አንድ የወይን ጠጅ ያለው በፍታ የለበሰ ባለጸጋ ሰው ነበር...አንድ ባለጸጋ ሰው ሞተ... አንድ ሰው ወደ ኢያሪኮ ወጣ. . .አንድ ባለጠጋ መጋቢ ነበር. . .የአንድ ሰው መሬት ብዙ አፈራለት. . . አንድ የታወቀ ሰው ወደ ሩቅ አገር ሄደ።

እንደ ኢየሱስ ዓይነት አስተማሪ ልሆን ወሰንሁ። የተለየ ወይም አዲስ መሆን አልፈለግሁም። ልክ የኢየሱስ ክርስቶስ ትክክለኛ ቅጂ የመሆን መሻት ውስጤ አደረ።

ታላቅ ሰባኪ የመሆን ቁልፉ ሌላ ታላቅ ሰባኪን መቅዳት ነው። አንድ የብዙዎችን ሕይወትና ኑሮ በአገልግሎቱ የዳሰሰ ሰባኪ ፈልግና እንደ እርሱ ሁን። እንዴት መስበክ እንደሚቻል በመቅዳት ተማር! ደረቅ ስለሆነው ስብከትህ ማንንም አትኮንን! ምን ማድረግ እንዳለብህ ታውቃለህ። በተመሳሳይ መንገድ ስበክ፣ አስተምር እናም ስኬትን ትጎናጸፋለህ። በዓይነትህ አዲስ ለመሆን አትጣጣር፤ ምክንያቱም ምንም አዲስ ነገር የለም።

"መቅዳት" አለብህ ስል ምን ያህል ግልጽ እንደሆነልህ አላውቅም። ታላላቅ ሰዎች ያደረጉት ነገር ቢኖር ያለ ሐፍረት መቅዳት፣ ፎቶ ኮፒ፣ ሪፕሌይ (መድገም) እንዲሁም ሪዋይንድ (ወደ ቀደመው መመለስ) ናቸው። በመጨረሻ የቀደመው አምሳያህን ሆነህ ራስህን ታገኘዋለህ።

ይህንን ለማድረግ ኩራት የሚተናነቃቸው ሰዎች የሌላው ቅጂ ሆነው መገኘታቸው አይቀርም። ስለ ምን ታዲያ የምታደንቀውን ሰው ለመቅዳት አትመርጥም? እግዚአብሔር እንዲያሠለጥንህና እንዲመራህ ወደ ሕይወትህ የላከልህን ሰው ለመቅዳት አትሻም?